ልዩ ዕትም

# ወጋገን

# 18ኛ

## ዓመታዊ መጽሔት




18ኛ ዓመት

ወላይታ ልማት ማህበር
Wolaytta Dichaa Amuwaa
Wolaitta Development Association

የሰው ሃብት ልማት

ዘላቂ የኑሮ ማሻሻያ

የተቀናጀ ጤና አገልግሎት

Wolaytta Worqaa Mayzzana!

# የቆንቶ አባ ፓስካል ቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋም

በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ካፑቺን ማህበር የቆንቶ አባ ፓስካል ቴክኒክና ሙያ ማሠልጠኛ ተቋም በዘመናዊ መልኩ ከተቋቋመ በርካታ ዓመታትን አስቆጥረዋል። ቤተክርስቲያኒቷ ከስብከተ ወንጌል ጎን ለጎን ለሰው ልጅ ከምታበረክታቸው ዘርፈ ብዙ አገልግሎቶች ውስጥ የቴ/ሙ/ ማሠልጠኛ ተቋም አገልግሎት ዋንኛው ነው። ዓላማውም በስነ ምግባር የታነጸ ሠልጣኝን በማብቃት ራሱንና ሀገሩን የሚጠቅም ዜጋን ማፍራት ነው።



የቀድሞ የተቋሙ ተማሪ በአውቶ ኤሌክትሪክ ስራ ላይ

## ዕውቅና ባገኘንባቸው፡

- በአውቶሞቲብ ኢንጂን ሰርቪሲንግ ከደረጃ 1 - 4
- በጀነራል ሜታል ፋብርኬሽን ከደረጃ 1 - 4
- በኤሌክትሪካል ማሽን ድራይብ ቴክኖሌጂ ከደረጃ
- ሳኒታሪ ኢንስታሌሽን (ኦንሳይት ኮንስትራክሽን) ከ



የኦንሳይት ኮንስትራክሽን ሠልጣኞች በተግባር ሥልጠና ላይ


በታወቁ እና ከፍተኛ የማስተማር ልምድ ባላቸው መምህራን ምቹ የመማሪያ ክፍሎች ለውድ ሠልጣኞቹ በንድፈ ሀሳብና በቂ የተግባር ስልጠና በመስጠት ላይ ይገኛል።
ያሠለጠንናቸው ሠልጣኞች በCoC ምዘና ያለ ምንም ስጋት ማለፍ የሚችሉ መሆናቸው ልዩ ያደርገናል።



የደረጃ 4 ሠልጣኞች በልምምድ ላይ


## በተጨማሪ የምንሠጣቸው አገልግሎቶች

- ሙሉ የመኪና ጥገና፣ የጎማ ባላንስ አላይንመንት ማድረግ
- ማንኛውንም የጣውላ ስራ (የቤትና የቢሮ ዕቃዎች.... )
- የብረታ ብረት ሥራ
- የብሎኬት ምርት ዋነኞቹ ናቸው።



ደረጃ 1 የኤሌክትሪክ ተማሪዎች የ CoC ምዘናን ካለፉ በኋላ

**አድራሻችን፡** ወላይታ ሶዶ ከነዳጅ ዲፖ ፊት ለፊት ባለው ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ ይገኛል።



የደረጃ 3 አውቶሞሚብ ስልጣኞች በተግባር ስልጠና ላይ



ደረጃ 1 የአውቶሞቲብ ሠልጣኞች በስልጠና ላይ



የኦንሳይት ሠልጣኞች በሥልጠና ላይ




የሳኒቴሪ ተማሪዎች በተግባር ስልጠና ላይ



አሰልጣኙ ለደረጃ 3 ሠልጣኝ የተግባር ሥልጠና ሲሰጥ


በወላይታ ልማት ማህበር ኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ማኔጅመንት ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ አ.አ.አ የ2018 ዓመታዊ መጽሔት (ልዩ ዕትም)
የካቲት 2011ዓ.ም

ፎቶግራፍ



አማኑዔል አይቻ
በኢንፎ/ኮሚ/ማኔ/ዳይ/ሕ/ዲ/ኦፊሰር

ዋና አዘጋጅ



ዘሪሁን ሎሪሶ
በኢንፎ/ኮሚ/ማኔ/ዳይ/ የኮሚዩኒኬሽን ቡድን መሪ

አርትዖት፣ ሌይ አዉት እና ግራፊክስ



ታምራት ማቴዎስ
ኢንፎ/ኮሚ/ማኔ/ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

# ወ ል ማ ወላይታ ልማት ማህበር

# WOLAITTA DEVELOPMENT ASSOCIATION

**ራዕይ፡** ከኋላቀርነትና ድህነት ፍጹም የተለወጠ ወላይታን ማየት ነው።

**ተልዕኮ** በወላይታ ህዝብ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ፣ የህዝቡን ንቁ ተሳትፎና ባለቤትነትን የሚያረጋግጥ፣ ከህዝቡ፣ ከግል ባለሃብቶች፣ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶችና ከለጋሽ የልማት አጋሮቻችን የሚሰበሰበዉን ሀብት ዉጤታማ በሆነ መልኩ በመጠቀም በሰው ሀብት ልማት፣ ዘላቂ ኑሮ ማሻሻያና በተቀናጀ ጤና የሚያተኩሩና የወላይታን ህዝብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት የሚያፋጥኑ ተግባራትን ማከናወን ነዉ።

**እሴቶች** አሳታፊነት፣ ግልጸኝነት፣ ተጠያቂነት፣ ውጤታማነት፣ ፍትሐዊነት፣ ጾታ እኩልነት እና አካታችነት

**የትኩረት አቅጣጫዎች፡**
1. የሰዉ ሀብት ልማት
2. ዘላቂ የኑሮ ማሻሻያ
3. የተቀናጀ ጤና አገልግሎት


ስልክ - +251-46-551-36-92
+251-465-51-21-88
+251-465-51-52-42
ፋክስ- +251-46-551-00-37
ፖ.ሳ.ቁ.:..........001 ወላይታ ሶዶ ኢትዮጵያ
ኢሜይል:info@wolaittada.org
ድረ-ገጽ: www.wolaittada.org
ማኅበራዊ ድረ-ገጾች:
www.facebook.com/wolaittadevelopmentassociation
www.youtube.com/WODA2001
www.twitter.com/wolaitta


WolayttaWorqaaMayzzana!



ወላይታ ልማት ማህበር
Wolaytta Dichaa Amuwaa
Wolaitta Development Association

ከ 1993 ዓ.ም ጀምሮ


ወላይታ ልማት ማህበር
Wolaytta Dichaa Amuwaa
Wolaitta Development Association

ወላይታ ልማት ማህበር
Wolaytta Dichaa Amuwaa
Wolaitta Development Association

Since 2000 G.C

ወላይታ ልማት ማህበር
Wolaytta Dichaa Amuwaa
Wolaitta Development Association

**Wolaytta Worqaa Mayzzana!**



# በውስጥ ገጾቻችን . . .

ወላይታ ልማት ማህበር ከትናንት
ወዲያ፣ ትናንት እና ዛሬ ------------ 13

1. የትኩረት አቅጣጫዎች ------------21

1.1 የሰው ሃብት ልማት

1.2 ዘላቂ የኑሮ ማሻሻያ

1.3 የተቀናጀ ጤና ልማት

2. የተቋማዊ ለውጥ ሥራዎች---------- 35

2.1 የሰዉ ሀብት አስተዳደርና ልማት

2.2 ቢዝነስ ልማት

2.3 ዕቅድ፣ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ

2.4 አባላት ልማትና ሀብት አሰባሰብ

2.5 ኢንፎርሜሽንና ኮሚዩኒኬሽን

# መግቢያ

አንባቢዎቻችን ሰላም ይብዛላችሁ! ይህ 18ኛው ዓመታዊ መጽሔታችን ልክ እንደከዚህ ቀደሙ በበጀቱ ዓመቱ የተከናወኑ ዓበይት የልማት ተግባራትን ለአባላት፣ አጋሮቻችንና ደጋፊዎቻችን የምናወራበት ልሳን ቢሆንም ልዩ ዕትም ያስባለን ምክንያት የማህበራችንን ጉዞ ከትናንት ወዲያ ትናንትና ዛሬ ብለን ከፋፍለን በመጠኑም ቢሆን የማህበራችንን ደፋ ቀናና አወይ ብሎ ጎንበስ ጉዞ እንደገናም ላለፉት 18 ዓመታት ቀና ብሎ የቆየበትን ዓመታት ለአንባቢያን መረጃ መስጠት የሚችል ይዘት ስላለው ነው።

የትውልድ ፍሰቱ ቀጥሏል፤ ዘመን አልፎ ዘመን ሲመጣ ክረምት አልፎ በጋም ሲመጣና ሲሄድ ትውልድ መወራረሱ አይቀሬ ነውና የዛሬ የዛሬን በተገቢው መንገድ ሰንዶ ለትውልድ ማውረስ ተገቢና የሁላችንም ኃላፊነት ቢሆንም ያለፈውንም ከምንጩ ቀድቶ ማስጎንጨት ሲያሻም እንደተገቢነቱ መልካም ዓርአያነት ማወደስና ዕውቅና እየሰጡ ማለፍ የራስ ኃላፊነትን በተገቢው ሳይወጡ ታሪክን የማያውቅ ትውልድ ተነስቶ የደሃ ጎጆን በእሳት አጋየ ብሎ በጥልቀት ሳያዩት በደምሳሳው ሲያልፉት አለባብሰው ቢያልፉ በአረም ይመለሱ እንዳይሆንና ትውልድንም በደፈናው ከመኮነን፣ ጣት ከመቀሳሰርም መደኛና ምክንያታዊ መፍትሔም ሊሆን ይችላል።

ለዚህም እኛ የዛሬ ተረኞች ዘመኑ በደረሰበት የመረጃ ፍሰት ስርዓት ልክ ባይሆንም እንደ አቅማችን የራሳችንን ድርሻ ለመወጣት አባቶቻችን የመሰረቱትንና ከ1957 - 1969 ዓ.ም የቆየውን ልማት ማህበር የከትናንት ወዲያው ብለን ከ1985 - 1990 ዓ.ም (የወጋጎዳ ልማት ማህበር ምስረታ) ደግሞ የትናንትናው እንዲሁም ከ1993 ዓ.ም ወዲህ ያለውን ጊዜ የዛሬው ወልማ ብለን አደራጅተናል፤ አያይዘንም በተለመደው መልኩ እ.አ.አ በ2018 በጀት ዓመት በማህበሩ ሦስት የትኩረት አቅጣጫዎቹ ከተከናወኑ በርካታ የልማት ተግባራት ዓበይት ተግባራትን ብቻ ለይተን እንደሚከተለው አቅርበንላችኋል፤ መልካም ንባብ!!

ከዝግጅት ክፍሉ!!

# መልዕክቶች



**አማኑኤል አብርሃም**

**የወላይታ ልማት ማህበር ስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ**

ልማት የጋራ ጥረት ውጤት ነው፡፡ ተባብሮ መስራት ማህበረሰባችን ያለበትን የጋራ ማህራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮችን ለመቅረፍ ዋንኛ መሳሪያ ነው፡፡ የወላይታ ህዝብ ትብብርን በተለያዩ መድረኮች ተለማምዷል፡፡ በደቦና መሰል የትብብር ኩነቶች በጋራ በመስራት ችግሮችን በመቅረፍና ምርትን ከፍ በማድረግ ይታወቃል፡፡

ወላይታ ልማት ማህበር ህዝቡ የዚህን ዓይነት ትብበር በዘመናዊ መልኩ ከሚተገብርባቸው መድረኮች አንዱ ነው፡፡ የወላይታን ህዝብ በማስተባበር ላለፉት 18 ዓመታት መንግስት የሚያከናውናቸውን የልማት ተግባራት በመደገፍ በአካባቢው ከፍተኛ ለውጥ እንዲመጣ የበኩሉን አስተዋጽኦ ሲያበረክት ቆይቷል፡፡

ልማት ማህበሩ ከምን ጊዜውም በላይ ባለፉት ሁለትና ሶስት ዓመታት ውስጥ ያስመዘገባቸው ውጤቶች የመላው አባላት የስራ ውጤት መሆኑን ሳንዘነጋ የልማት ማህበሩ ሰራተኞችና አመራሩ ምን ያህል ትኩረት ሰጥተው እየሰሩ እንደሆነም ማሳያ ነው፡፡

በተለይም በ2018 የበጀት ዓመት የተሰበሰበው ከ88 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ እና በወላይታ ሊቃ ት/ቤት የተመዘገበው ከፍተኛ ውጤት ልማት ማህበራችን ከየትኛውም ጊዜ በላይ በተሻለ የስራ ሞራልና ጥንካሬ ላይ እንደሚገኝ ያረጋግጣል፣ ይንን ስኬታችንን ይበልጡን አጠናክረን ማስቀጠል እንችል ዘንድ እስከዛሬ ያለምንም ስስት ከጎናችን በመሆን ያበረከታችሁል ዕውቀታችሁ፣ ጊዜያችሁና ገንዘባችሁ ለወደፊትም ተጠናክሮ እንዲቀጥል በልማት ማህበሩ ቦርድ ስም ጥሪዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም ልማት ማህበሩ ከስትራቴጂክ ዕቅዱ የማህበረሰብ ልማት ሕንጻ ግንባታን ጨምሮ እ.ኤ.አ. ለ2019 በጀት ዓመት ለያዛቸው ሌሎች ግዙፍ ፕሮጀክቶችና የልማት ዕቅዶች እንዲሁም ባለፈው በጀት ዓመት በተላለፈው ውሳኔ መሰረት ማህበሩ ከሰበሰበው ሃብት ገሚሱ ሃብቱ በተሰበሰበበት አካባቢ ፍላጎት መነሻነት በማህበሩ የትኩረት አቅጣጫዎች መሰረት ተግባራዊነቱ እንዲረጋገጥ ሁሉም አባላት በተለመደው የስራ ወኔና ቁርጠኝነት በመነሳት በአንድነት ከግብ ለማድረስ እንድንሰራና ከድህነትና ኋላቀርነት ፍጹም የተለወጠ ወላይታን የማየት ራዕይ ስኬት የበኩላችንን አስተዋጽኦ እንድንወጣ ለሁሉም የማህበሩ አባላትና ደጋፊዎች አደራ እላለሁ፡፡ አመሰግናለሁ!

Wolaytta Worqaa Mayzzana!

# የፎቶ ገበታ




በዳሞታ ኮንስትራክሽ ኩባንያ እየተገነባ የሚገኘው የተሻሻለው ባለ 9 ወለል
የዎላይታ ማህበረሰብ ልማት ሕንጻ ዲዛይን (ወላይታ ሶዶ ከተማ)




በዳሞታ ኮንስትራክሽ ኩባንያ እየተገነባ የሚገኘው ባለ 9 ወለል
የዎላይታ ማህበረሰብ ሕንጻ (ወላይታ ሶዶ ከተማ)




**ሀብታሙ ጢሞቲዎስ**
**የወላይታ ልማት ማህበር ዋና ዳይሬክተር**

ውድ የወላይታ ልማት ማህበር አባላት፣ ደጋፊዎችና አጋሮቻችን ልማት ማህበራችን ባለፉት 18 ዓመታት ጉዞ የህብረተሰባችንን በርካታ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግሮችን አቅም በፈቀደ መጠን ሲፈታ ቆይቷል፡፡

ልማት ማህበሩ በእነዚህ ዓመታት ከሕዝብ የሚሰበሰብ ሃብት በአግባቡ በመጠቀም በትምህርት ጥራትና ተደራሽነት፣ በጤና፣ በንጹህ የመጠጥ ውሃ ተደራሽነት፣ በዘላቂ የኑሮ ማሻሻያና አካባቢ ጥበቃ የብዙ መቶ ሺህ የህብረተሰባችን ክፍሎች ኑሮ ደረጃ በማሻሻል ከመንግስትን ጎን በመሆን የራሱን ድርሻ ሲያበረክት ቆይቷል፤ በዚህም ብዙ ተጨባጭ ስኬቶችን አስመዝግቧል፡፡ ማህበሩ ያለአባላት ተሳትፎ የልማት ውጥኖች ከግብ ማድረስ አይችልም ነበር፤ ለዚህም ከፍተኛ ምስጋና ያቀርባል፤ ለቀጣይ ጊዜያትም ከጎናችን እንድትሆኑ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ከአባላት በተጨማሪ አጋሮቻችን ያደረጉልን ድጋፍ ለዕቅዶቻችን መሳካት ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፤ ልማት ማህበራችን ከ2016-2020 እ.ኤ.አ ላሉት ዓመታት ለያዘው ስትራቴጂክ ዕቅድ ከፍተኛ በጀት ያስፈልገዋል፡፡ ይህ በጀት ደግሞ ከማንም የሚመጣ ሳይሆን ቀና ልቦና ካላቸው በጎ አድራጊ አባላቶቻችን እና ለጋስ አጋሮቻችን ነው፡፡

በዞናችን ውስጥ እና ከዞናችን ውጭ በተደረገው የአባላትና ደጋፊዎች ንቅናቄ ሁሉም አባሎቻችን ለልማት ማህበሩ በየእኔነት ስሜት ያሳያችሁት አጋርነት የሚደነቅ ነው፤ ይህ አጋርነታችሁ እንዲጠናከርም በንቅናቄው ወቅት ከእናንተ ለተነሱ አስተያየቶችና ጥያቄዎች ዋጋ ሰጥተን በመስራት ለመጪው ጊዜ ከአባላት ጋር ያለውን ግንኙነት ለማጠናከር ልማት ማህበሩ ቃል ይገባል፡፡ እስካሁን ባደረግነው ርብርብ ሁሉ ከጎናችን ላልተለያችሁን ሁሉ በልማት ማህበሩ ስም ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

የሰላምና መልካም የስራ ዘመን ይሁንልን!
Wolaytta Worqaa Mayzzana!!!

# ወላይታ ልማት ማህበር ከትናንት ወዲያ፣ ትናንት እና ዛሬ

## ሀ. ወልማ ከትናንት ወዲያ፣

ሰኔ 13/1957 ዓ.ም. በሶዶ ከተማ ከፍተኛ የህዝብ ጉባኤ ተካሂዶ ነበር፡፡ ይህ ጉባኤ የተጠራውና የተመራው በደጃዝማች ወልደሰማያት ገብረወልድ፣ የወላይታ አውራጃ ገዥ ነበር፡፡ የጉባኤው ተሳታፊዎችም የተጠሩት ከመላው ወላይታና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ነው፡፡ ይህ ህዝቡ ለልማት ያለውን ቁርጠኝነት ያሳየበት ጉባኤ ነው፡፡

ይህ ጉባኤ የመጀመሪያው የወላይታ ልማት ማህበር መስራች ጉባኤ ነበር፡፡ በጉባኤው ደጃዝማች ወልደሰማያት ገብረወልድ በማህበሩ ሰብሳቢነት ተመርጠዋል፡፡ እንደዚሁም ከእያንዳንዱ ወረዳ ሰባት ተወካዮች ያሉት አርባ ዘጠኝ አባላትን የያዘ የልማት ኮሚቴ አባላት ተመርጠዋል፡፡

ይህ የምስረታው ጉባኤ ኮሚቴ በመምረጥ ብቻ አላበቃም፤ የወደፊት የማህበሩ የጉዞ አቅጣጫም ሆነ በገቢ ምንጭ ዙሪያ መክሯል፤ ስብሰባው ህዝቡ የራሱን ችግር በራሱ ለመፍታት የወሰነበትና ያመነበት ነበር፡፡

በዚህ መነሻ አርሶ አደሩ፣ ነጋዴው፣ መንግስት ሰራተኛው እና ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል በጉልበቱ፣ በማቴሪያልና ገንዘቡ ወላይታ የሚበለጽግበት ሁኔታ መፍጠር እንዳለበት ታመነ፡፡ በመሆኑም ገንዘብ መዋጣት እንዳለበት ተወሰነ፡፡

የመዋጮ መጠንም የመንግስት ሰራተኛ ከደመወዙ 15%፣ አርሶ አደር በመሬት ግብሩ ላይ 30%፣ ከአንድ ኩንታል ቡና ሽያጭ ብር 2፣ ከአንድ ጋማ ከብት ሽያጭ ብር 2፣ ከአንድ ቀንድ ከብት ሽያጭ ብር 1 ለልማቱ እንዲከፈል ጉባኤው ተስማምቷል፡፡

በዚህ ጉባኤ የተመሰረተው የቀድሞ ወላይታ ልማት ማህበር እስከ 1963 ዓ.ም. ድረስ ለልማት ተግባር የሚውል ከ1.2 ሚሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ከህዝብ ሰብስቧል፤ በዚህ በተሰበሰበው ገንዘብ ለልማት ተግባር የሚያገለግሉ ማሽኖች (ዶዘር፣ ግሬደር፣ ሎደር፣ ወዘተ...) ተገዝቷል፡፡

በዚህ ወቅት ማህበሩ በተገዙ ማሽኖችና ከህዝብ በተሰበሰበውና በዕርዳታ በተገኘው ገንዘብ በርካታ የልማት ስራዎች በትምህርት፣ በጤና፣ በመንገድና በሌሎች ዘርፎች አከናውኗል፡፡ በስራው የህዝቡ ተሳትፎ በገንዘብ ብቻ ሳይሆን በማቴሪያል ድጋፍና በጉልበትም ከፍተኛ ነበር፡፡

የከትናንት ወዲያው ወልማ ከ1963 ዓ.ም. ጀምሮ እንቅስቃሴው እየተዳከመ ሄደ፡፡ ማህበሩ እስከ 1963 ዓ.ም. የዘለቀ ቢሆንም መጠነኛ የሆኑ የቀድሞ ፕሮጀክቶችን የመጠገንና የመከለስ ስራ ሲያከናውን ነበር፡፡ ለእንቅስቃሴው መቀነስም በዋናነት የሚጠቀሰው የደጃዝማች ወልደሰማያት ገብረወልድ ከአውራጃው መዛወራቸው ነው፡፡

በዚህም የተነሳ ለልማቱ እንቅስቃሴ ምንም ትኩረት አልተሰጠም፤ ቀደም ሲል እንደነበረው የአውራጃው ገዥ የልማቱን ስራ መምራት ቀርቶ ተራ ድጋፍ እንኳ ተነፍጎ ነበር፡፡ በእነዚህ ምክንያቶች ሲዳከም የመጣው ልማት ማህበር ደርግ ወደ ስልጣን በመምጣቱ በ1969 ዓ.ም. ፍጹም እንዲከስም ተደረገ፡፡ ንብረቶቹም በተለያየ አካባቢ እንዲበተኑ ተደረገ፣ የህዝቡ የልማት ራዕይ ጨለመ፤ ይሁን እንጂ የወላይታ ህዝብ ልማት ማህበሩ ሲፈርስበት "እሺ" ብሎ ተቀብሎ አልተቀመጠም ነበር፡፡

## ለ. የትናንቱ ወልማ

መጋቢት 1985 ዓ.ም. ዳግም ተመሰረተ፡፡ ይሁንና ማህበሩ የወላይታ ህዝብ የልማት ፋላጎትን ለማሟላት የገባውን ቃል ከመፈጸም ይልቅ ዕቅዱን በወረቀት ከማስፈር በላይ እስከ 1988 ዓ.ም. ድረስ ይህ ነው የሚባል የረባ ስራ አልሰራም፡፡ በ1988 ዓ.ም. በአዋሳና ሶዶ ከተማ በተደረገው የህዝብ ጉባኤ ማህበሩ የተሻለ አቅጣጫ እንዲይዝ ተደረገ፡፡ የማህበሩ እንቅስቃሴ በጉባኤው ተገምግሞ ማስተካከያ ተበጀለት፡፡ በዚህ ማግስት ከደቡብ ክልል ፍትህ ቢሮ የምስክር ወረቀት አገኘ፡፡ እንደዚሁም ከክልሉ አደጋ መከላከልና ዝግጁነት ኮሚሽን የስራ ፈቃድ አገኘ፡፡

በዚህ ወቅት ማህበሩ ነፍስ ዘራና በየወረዳው ለህዝቡ ጥያቄ ምላሽ መስጠት ጀመረ፤ የልማት ፕሮጀክቶችን በየአካባቢው መስራት ጀመረ፡፡ በየወረዳው በሚገኙ የማህበሩ ጽ/ቤቶች በቋሚነት የኮሚቴ አባል ተመድቦ እንዲሰራና ህዝቡን በወጉ ለልማት ማስተባበር ጀመረ፡፡ ማህበሩ እንቅስቃሴውን አጠናክሮ በጀመረበት በዚህ ወቅት የ"ወጋጎዳ" (ወላይታ፣ ጋሞ፣ጎፋና ዳውሮ) ልማት ማህበር ምስረታ መጣ፡፡

በህዳር 1990 ዓ.ም. ወጋጎዳ ልማት ማህበር በሰሜን ኦሞ ዞን ውስጥ የነበሩ ወላይታ፣ ጋሞጎፋ፣ ዳውሮ ኮንታ ልማት ማህበራትን በማዋሄድ ተመሰረተ፡፡

ይህ ቅይጥ ማህበር እንደተመሰረተ በቀድሞ ወልማ እጅ የነበረው ንብረትም ሆነ ገንዘብ ባጠቃላይ ማንኛውም ነገር እንዳይንቀሳቀስ ከሰሜን ኦሞ ዞን አስተዳደር በተሰጠው ትዕዛዝ እንቅስቃሴው ተገታ፡፡
ከሰሜን ኦሞ ዞን አስተዳደር ፋይናንስ መምሪያ ሁለት የሂሳብ ባለሙያ የያዘ ቡድን ተልኮ የወልማ ሂሳብና ንብረት ተመርምሮ በሶዶ የሚገኘው የወልማ ዋና ጽ/ቤት በጥር 1990 ዓ.ም. ተዘግቶ ሰራተኞቹ ወደ “ወጋጎዳ” ልማት ማህበር አርባምንጭ እንዲዛወሩ ተደረገ፡፡
በጊዜው የወልማ ንብረት ወደፊት ወደ ወጋጎዳ ልማት ማህበር ይተላለፋል ተብሎ በጽ/ቤቱ ውስጥ ታሽጎ ሲቀር በኢት/ያ ንግድ ባንክ ወላይታ ሶዶ ቅርንጫፍ የነበረው ገንዘብ ግን ያለቀጠሮና ያለወልማ ኮሚቴ እውቅና ወደ ኢት/ያ ንግድ ባንክ አርባምንጭ ቅርንጫፍ ወደሚገኘው ወደ ወጋጎዳ ልማት ማህበር በሰሜን ኦሞ ዞን አስተዳደር ትዕዛዝ እንዲዛወር ተደረገ፡፡ በዚህም ምክንያት ወልማ ዳግም ፈረሰ፡፡
ከላይ በተዘረዘሩ ምቹ ባልሆኑ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች በተደጋጋሚ ቢፈርስም በእነዚህ ጊዜያት በአጠቃላይ ከ1957 ከምስረታው ማግስት ጀምሮ እስከ ዳምግ መቋቋሙ ብስራት ዋዜማ ድረስ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት አከናውኗል፡፡

- 25 ክፍል ያላቸውን የመንግስት መስሪያ ቤቶችን በቀድሞ ወላይታ አውራጃ ሰባቱም ወረዳዎች አስገንብቷል፤
- ከስዊድን ተራድኦ ድርጅት /SIDA/ ጋር በመተባበር 15 ት/ቤቶችን አስገንብቷል፤
- በ18 አብያተክርስቲያናት 18 ት/ቤቶችን በመገንባት ለቤተክርስቲያናቱ አስረክቧል፤
- 21 ክፍሎች ያሏቸውን 5 ክሊኒኮች በማስገንባት ለጤና ጥበቃ ሚኒስቴር አስረክቧል፤
- በቦዲቲና ሁምቦ ጠበላ ከተሞች የንጹህ መጠጥ ውሃ መስመር ዝርጋታ አከናውኗል፤
- በሶዶ ከተማ የቁራ አገልግሎት መስጫ እና ወወክማን አስገንብቷል፤
- የመሬት ጥበት ካለባቸው ከተለያዩ የወላይታ አውራጃዎች 500 አርሶ አደሮችን አበላ (ሁምቦ ወረዳ) ወስዶ እንዲሰፍሩ አድርጓል፤
- 503 ኪ/ሜ ርዝመት ያለውን የጥርግያ መንገድ አሰርቷል፤
- 2 የብረትና 25 የእንጨት ድልድዮችን አስገንበቷል፤ ከነዚህ ውስጥ ዳውሮን ከወላይታ ሲያገናኝ የቆየው የ42 ሜትር ርዝመትና የ4ሜትር ስፋት ያለው የኦሞ ድልድይ ተጠቃሽ ነው፡፡

## ሐ. የዛሬው ወልማ

ምንም እንኳን ማህበሩ በወቅቱ የነበረው የፖለቲካ አስተዳደር በሚያራምደው ርዕዮት በተደጋጋሚ እንዲፈርስ ቢደረግም ከደረሰው በደልና በነበረው ምቹ ያልሆነ አስተዳደር ተስፋ በማይቆርጡ የልማት ጀግኖች ለሦስተኛ ጊዜ ህዳር 1993 ዓ.ም. በዞን ደረጃ ዳግም እንዲዋቀር ተደረገ፡፡
የዞኑን መዋቅር ተከትሎ በታህሳስ 15/1993 ዓ.ም. በተካሄደው ከፍተኛ የህዝብ ጉባኤ የአዲሱ ወልማ ምስረታ ለሶስተኛ ጊዜ እውን ሆነ፤ ታሽጎ የነበረው የማህበሩ ጽ/ቤትም ዳግም እንዲከፈትና ስራ አስኪያጅ እንዲቀጠር ተወስኖ በወርሃ ጥር 1993 ዓ.ም. ለሶስተኛ ጊዜ አንሰራርቶ ሕይወት ዘርቶ አገልግሎት ጀመሯል፤ ከ1993-2003 ዓ.ም. ባሉት አስር ዓመታትም ቀድሞ በተዋቀረበት ጽኑ መሰረት ቀጥሎ በዞኑ ሁሉ አቀፍ ልማትና ለውጥ ዓላማው አድርጎ የተነሳበትን ለማሳካት የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት አከናውኗል፡፡

### 1. በግብርናና አካባቢ ጥበቃ ዘርፍ፡

- አካባቢን ለመጠበቅ በሶዶ ከተማ ባሉ 1ኛና 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የሚገኙ ተማሪዎችንና በአካባቢው የሚገኙ አርሶ አደሮችን በማስተባበር የዳሞት ተራራን ተፈጥሮ ጠብቆ ለማቆየት ከ32,000 (ሰላሳ ሁለት ሺ.ህ) የሚበልጥ የዝግባ፣ አበሻ ጥድና ግራቪሊያ ችግኞች አስተክሏል፡፡
- ለአርሶ አደሮች 5,000 የአፕል ችግኞችን አሰራጭቷል፤
- በቦሎሶ ሶሬ ባዳዬ ቀበሌ አንድ የእንስሳት ጤና ኬላ አስገንብቷል፤

### 2. በትምህርት ጥራትና ተደራሽነት ዘርፍ፡

- በሶስት ወረዳዎች (ሶዶ ዙሪያ፣ ቀድሞ ኪንዶ ኮይሻ (አሁን ዳሞት ሶሬ) እና ኦፋ ) 4 ትምህርት ቤቶችን አስገንብቷል፡፡ (ሶዶ ዙሪያ ወረዳ በቅሎ ሰኞና ሾላ ኮዶ 1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ ዳሞት ሶሬ ወረዳ ዶጌ ላሮሶ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት፣ ኦፋ ወረዳ ኦሜ ቦሎላ 1ኛ ደረጃ ት/ቤት

- በቀድሞ ሰባቱም የወላይታ ዞን ወረዳዎች 4 እና 8 ክፍል ያላቸውን የተማሪዎች መማሪያ ህንጻዎች፣
- ቤተሙከራና ቤተመጽሐፍት ያሉበት የት/ቤቶች ማስፋፊያ ግንባታ አካሂዷል፡፡ በእነዚህ ግንባታዎች በየዓመቱ በአማካይ 17,280 ተማሪዎች ተጠቃሚ እንዲሆኑ አድርጓል፤
- በሁምቦ ወረዳ (አንካ ወቻ እና አበላ ጋፋታ ት/ቤቶች) እና በዳሞት ጋሌ ወረዳ ሀርቶ ቡርቅቶ ት/ቤት 32 መምህራንን ተጠቃሚ ያደረገ መጠለያ ቤት ግንባታ አካሂዷል፤
- ለአስር ት/ቤቶች የወንበር፣ ጠረጴዛ፣ የተማሪ ዴስክ እና መደርደሪያዎች እጥረት ለመቅረፍ አሰርቶ በድጋፍ አበርክቷል፤
- ለስምንት 2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የማጣቀሻ መጻህፍት እና የኮምፒውተር ድጋፍ አድርጓል፤
- በሶዶ ከተማ ደረጃውን የጠበቀ አንድ ባለ ሁለት ወለል የሕዝብ ቤተመጻህፍት ህንጻ ገንብቷል፤ የውስጥ ቁሳቁሶችንም አሟልቶ ለመንግስት አስተላልፏል፡፡
- 700 ተማሪዎችን (ከ1ኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ ድረስ ያሉ) የትምህርት ወጪ በመሸፈን፣ የትምህርት ግብዓት መሳሪያዎችን ድጋፍ በመስጠትና የህክምና ወጪያቸውንም በመሸፈን የተሻለ መሰረት እንዲኖራቸው አድርጎ አስተምሯቸዋል፤
- 236 በ2ኛ ደረጃ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎችን ሽልማት በመስጠት አበረታትቷል፤

## 3. በተቀናጀ የሕብረተሰብ ጤና አገልግሎት፡

- 6 ደረጃቸውን የጠበቁ የጤና ኬላዎች በ6 ቀበሌዎች አሰርቷል (ብላቴ ኤታ፣ ፋንጎ ቦሎሶ፣ ሙንደና፣ ዜሬዳ፣ አፋማ ሚኖ፣ እና አባያ ጮካሬ) ለጤና ኬላዎቹ የህክምና መሳሪያዎች፣ መድሃኒትና እና ፊርኒቸር ድጋፍም ሰጥቷል፡፡ ባለሙያዎችንም ለስድስት ወራት አሰልጥኖ በየጤና ኬላዎቹ ተመድበው እንዲሰሩ አድርጓል፤
- ለዕድር ዳኞች፣ ለሃይማኖት መሪዎች፣ ለወጣቶችና ሴቶች ማህበራት ተወካዮች፣ ለፀረ ኤድስ ክበብ ተወካዮች፣ ለሴተኛ አዳሪዎች፣ለወረዳ አመራር አካላት እና ቀበሌ አስተዳደሮች በኤች.አይ.ቪ./ኤድስ መከላከል የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ወርክሾፖችና ስልጠናዎችን ሰጥቶ በሽታውን በመከላከል ረገድ የራሳቸውን ድርሻ እንዲወጡ አድርጓል፤
- ከሶዶ ዙሪያ ወረዳ ለተወጣጡ 50 ወጣቶች የማህረሰብ ዉይይት አመቻችነት ስልጠና ተሰጥቷል፤
- በቀድሞው ወላይታ ዞን በሚገኙ ሰባቱም ወረዳዎች 12 የፀረ ኤድስ ክበባትን አደራጅቷል፤ የተለያዩ ማስተማሪያ መሳሪያዎችንና ጽሑፎችን ድጋፍ አድርጓል፤
- ለ130 ኤች.አይ.ቪ. ፖዜቲቭ ለሆኑ ግለሰቦች የቀለብ እህል ድጋፍና ህክምና አገልግሎት ድጋፍ አድርጓል፤ የምክር አገልግሎትም ሰጥቷል፤
- በዳሞት ጋሌ እና ቦዲቲ ከተማ ወጣቶች አስተባባሪነት ችግኝ ተከላ አካሂዷል፤ የጸረ ኤች.አይ.ቪ. ቅስቀሳ ት/ት አድርጓል፡፡ በዚህም ህብረተሰቡ ስለበሽታው ያለው ግንዛቤ እንዲዳብር አድርጓል፤

## 4. በዘላቂ የኑሮ ማሻሻያ ዘርፍ፡

- 22 ጎዳና ላይ የሚኖሩ ወጣቶችን እንደየዝንባሌያቸው በግንባታና አውቶ መካኒክስ የሙያ መስኮች በሶዶ ቴክኒክና ሙያ ማሰልጠኛ ማዕከል አሰልጥኖ የሙያ ባለቤት አድርጓቸዋል፤
- በዳሞት ጋሌ ወረዳ በህብረት ስራ የተደራጁ ወጣቶችን አቅም ለመገንባት መነሻ ካፒታል ተዘዋዋሪ ብድር በመስጠት ኢኮኖሚያቸውን እንዲያሻሽሉ ተደርጓል፤
- ለ15 አቅመ ደካማ ግለሰቦች በሶዶ ከተማ አስተዳደር የመኖሪያ ቤት ሰርቶ ሰጥቷቸዋል፤
- በሁምቦ ወረዳ አባያ ዙሪያ አካባቢ ለሚገኙ መኖሪያ ቤታቸው ለተቃጠለባቸው 138 አባወራዎች 46 ብሎክ ቤቶችን ገንብቶ አስረክቧል፤
- በአባያ ሀይቅ ዙሪያ በአሳ ማስገር ህብረት ስራ ማህበራት ለተደራጁ 60 ወጣቶች ብር 30,000 (ሰላሳ ሺህ) ተዘዋዋሪ ብድር ተሰጥቶ ውጤታማ እንዲሆኑ አስችሏል፤
- 130 አካል ጉዳተኞችን የማቋቋም፣ እንስሳት እርባታና ሰብል ልማት ተግባር ተኮር ስልጠና በመስጠት የወተት ላም እና የእርሻ በሬ ተሰጥቷቸው ኑሯቸውን እንዲያሻሽሉ አድርጓል፤
- በሙንዴና (ኪንዶ ኮይሻ ወረዳ) እና ብላቴ ኤታ (ድጉና ፋንጎ ወረዳ) ቀበሌዎች የመጠጥ ውሃ ሰርቶ የአካባቢው ህዝብ ከውሃ ችግር እንዲላቀቅ አድርጓል፤

## ወልማ ከ2003- እስከ አሁን

### 1. በሰው ሃብት ልማት

- የወላይታ ሊቃ ት/ቤት በማቋቋም በትምህርት አቀባበላቸው የተሻሉ ሆነው የት/ቤቱን መግቢያ ፈተና ወስደው ያለፉ በድህነት ምክንያት ትምህርታቸውን በተገቢው መከታተል ያልቻሉ እና ወላጅ አጥ የሆኑ ተማሪዎችን ከ5-12ኛ ክፍል ሲያስተምር ቆይቷል፤ እያስተማረም ይገኛል።
- በወላይታ ሊቃ ት/ቤት ቅጥር ግቢ 1 ዘመናዊ የአይ.ሲ.ቲ. እና ቴክኒካል ድሮዊንግ ማዕከል የመገንባትና የውስጥ ቁሳቁሶችን የማሟላት ስራ ሰርቷል፤
- በወላይታ ዞን ውስጥ የሚገኙ ከ100 በላይ ት/ቤቶችን የትምህርት መሳሪያዎች፣ የቤተሙከራ ዕቃዎች፣ ማጣቀሻ መጻህፍት እና ሌሎች የትምህርት ግብዓቶችን በመደገፍ አደራጅቷል፤
- ከ7500 በላይ የድሃ ድሃና ወላጅ አጥ የሆኑ ተማሪዎችን ከ1ኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርሲቲ አስተምሯል፤ እያስተማረም ይገኛል፤
- የቅድመ መደበኛ ትምህርትን ለማሻሻል በቦሎሶ ሶሬ ወረዳ 6 ዘመናዊ የቅድመ መደበኛ ማዕከላትን አስገንብቷል፤ ሙሉ የሞንቶሶሪ ቁሳቁሶችን በማሟላት ለወረዳው አስረክቧል፤
- በቅደመ መደበኛና መደበኛ ትምህርትን በሚመለከት ለትምህርቱ ዘርፍ ባለድርሻ አካላት በርካታ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎች ሰጥቷል፤
- ወላጆቻቸዉን ላጡና በድህነት ምክንያት ዕድሜያቸው ከ9-14 ዓመት የሆኑ ከ13,900 በላይ ሕጻናት በተለያዩ ወረዳዎች በተከፈቱት የማስተማሪያ ማዕከላት በአመቻች መምህራን አማካይነት ከደረጃ 1-3 ድረስ የሚሰጣቸውን መደበኛ ትምህርት ለተማሪዎች የሚያስፈልገዉን ሙሉ የትምህርት ቁሳቁስ በማሟላት አስተምሯቸዋል፤
- ከ1,980 በላይ የሆኑ በትምህርት ዘርፍ ከፍተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ተማሪዎች፣ መምህራን፣ ርዕሰ መምህራን እና የትምህርት ባለሙያዎች የማበረታቻ ሽልማት ሰጥቷል፤
- ከአቅም ማነስ የተነሣ የ2ኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ለመከታተል አዳጋች ለሆነባቸው 108 ሴት ተማሪዎች ትምህርታቸውን ሳያቋርጡ እንዲከታተሉ ድጋፍ አደርጓል፤
- በዞናችን 11 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚሰጠውን ትምህርት በቴክኖሎጂ የታገዘ ለማድረግ 343 ክሮም ቡክ ኮምፒውተሮች፣ 11 server፣ 11 LCD፣ 330 Headset ተሰራጭቶ ስለአጠቃቀሙም ለየት/ቤቶቹ የትም/አመራሮችና መምህራን ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል፤
- ልማት ማህበሩ በሶዶ ከተማ የተለያየ የኢኮኖሚ ችግር ላለባቸውና የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቅ ላልቻሉት ተማሪዎች ከየአካባቢው መልምሎ በቀን፤ በማታ እና በርቀት ትምህርታቸውን እንዲቀጥሉ የተለያየ ድጋፍ አድርጓል፤
- አንድ የወላይታ ህዝብ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ የታሪክ መጽሐፍ አሳትሞ ለንባብ አብቅቷል፤
- የወላይታ ድቻ ስፖርት ክለብን በማቋቋምና በመምራት ስፖርቱን ለማሳደግ የራሱን ሚና ተጫውቷል፤ የአካባቢውን መልካም ገጽታም በሰፊው አስተዋዉቋል፤
  በቦዲቲ ከተማ አስተዳደር እና ዳሞት ጋሌ ወረዳ 2 የወጣት ማዕከላትን ለማጠናከር የቁሳቁስ ድጋፍ ሰጥቷል፤
- የወላይታ ዎጌታ ኤፍ.ኤም. 96.6 ሬዲዮ ጣቢያ በማቋቋም በተከታታይ በተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ርዕሰ ጉዳዮች እያዝናኑ የሚያስተምሩ መረጃዎችን በማቅረብ የዞናችንን ህብረተሰብ በመረጃ ለማዳበር ብርቱ ጥረት እያደረገ ይገኛል፤

### 2. በዘላቂ የኑሮ ማሻሻያ

- የሕብረተሰቡን ኑሮ ይበልጥ ለማሻሻል ከብር 5.1 ሚሊዮን በላይ ተዘዋዋሪ ብድር ለ17 ህብረት ሥራ ማህበራት ተሰጥቷቸው ወደ ስራ ገብተዋል፤
- የህብረት ስራ ማህበራትን ለማጠናከርና በስራ ዉጤታማ ለሆኑት በእንስሳት የሚሳቡ ተሽከርካሪዎችን ከነሙሉ ዕቃቸው ጋር አበርክቷል፤
- ለበርካታ አርሶአደሮች በንብ ማነብ ዙሪያ ስልጠና ከተሰጠ በኋላ ዘመናዊ የጀርመንና የኬንያ የንብ ቀፎዎችን ገዝቶ ሰጥቷል፤
- በሐር ትል አመራረት ለተሰማሩ ህብረት ስራ ማህበራት ስልጠና በመስጠት የመመገቢያ ዕቃዎች (feeding frame) ገዝቶ አበርክቷል፤

- የወላይታ ጉታራ ስልጠና ማዕከልን በቀጣይነት የማደራጀትና የማጠናከር ስራ በመስራት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል፤
- በሁምቦ ወረዳ በአምፖ ኮይሻ ቀበሌ የዘር ማባዣ ሰርቶ ማሳያ ስልጠና ማዕከልን በማቋቋም የተለያዩ ዘሮች ችግኞችን በማፍላት በአካባቢ ጥበቃ ስራ የራሱን ሚና ተጫውቷል፤ ማዕከሉን ሞዴል የስልጠና እና ሰርቶ ማሳያ ማዕከል ለማድረግም ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ይገኛል፤
- ለአርሶ አደሮች የተለያዩ የእርሻ መሳሪያ ግብዓቶች፣ የጓሮ አትክልቶች እና ፍራፍሬ ችግኞችን በመስጠት የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፤
- ለህብረት ስራ ማህበራት የንግድ ስራ ክህሎት ስልጠና በመስጠትና መነሻ ካፒታል በተዘዋዋሪ ብድር በመስጠት 4780 የዞናችንን አርሶ አደሮች ኢኮኖሚያቸውን እንዲያጠናክሩ አድርጓል፡፡
- በኦፋ ወረዳ ለሚገኙ ህብረት ስራ ማህበራት 1 የዘር ባንክ ገንብቷል፤
- በሶዶ ዙሪያ፣ ሁምቦ እና ኦፋ ወረዳ ለሚገኙ በህብረት ስራ ለተደራጁ 3 ማህበራት 300 ሺህ ብር ተዘዋዋሪ ብድር በመስጠት ትርፋማነታቸው እንዲሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክቷል፤
- ለ663 ማይክሮ ኢንተርፕረነሮች ተዘዋዋሪ ብድር ሰጥቷል፤
- በኦፋ ወረዳ ዳቀያ ቀበሌ 1 መስኖ ቦይ በመጠገን አገልግሎት እንዲሰጥ አድርጓል፤
- በኦፋ ወረዳ 10,000 ህዝብን ተጠቃሚ ያደረገ የወዮ ድልድይ ገንብቶ የአካባቢውን ህዝብ የትራንስፖርት ችግር ቀርፏል፤
- ለምግብ እጥረት ለተጋለጡ ከ1000 በላይ ሕጻናት የአልሚ ምግብ ድጋፍ ተደርጓል፤
- በሶዶ ከተማ የ10.7 ኪ.ሜ. ውስጥ ለውስጥ አስፓልት መንገድ ግንባታ አድርጓል፤
- በዝንጅብልና እንሰት አመራረት ላይ ከወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የተለያዩ የምርምር ስራዎችን ሰርቷል፤
- በኦፋ ወረዳ 7 ምንጮችን የማጎልበት ስራ ተሰርቶ ህብረተሰቡ ንጹህ የመጠጥ ውሃ እንዲያገኝ ተደርጓል፤

## 3. በተቀናጀ ጤና

- በአካል ጉዳተኝነት፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርቶችን በመስጠት የህብረተሰቡ ግንዘቤ እንዲዳብር ተደርጓል፤
- ለ124 ከኤች.ኤ.ቪ/ኤድስ ጋር ለሚኖሩ ግለሰቦች የህክምናና የአልሚ ምግቦች ድጋፍ አድርጓል፤
- ለ10,800 አካል ጉዳተኞች የሕክምና ድጋፍ ሰጥቷል፣ ኢኮኖሚያቸውን የማጠናከር ስራ ተሰርቷል፤ የቤት ለቤት ተሃድሶ አገልግሎትም ተሰጥቷቸዋል፡፡
- ልማት ማህበሩ የጤናውን ትምህርት ተደራሽ ከማድረግ አኳያ በወላይታ ማህበረሰብ ሬዲዮ ምጌታ ኤፍ ኤም 96.6 እና በሌሎች ሚዲያዎች የጤና ትምህርቶች ፕሮግራሞች እንዲተላለፉ አድርጓል፤
- በተለያዩ ጤና ጣቢያዎችና በቀበሌያት ተላላፊና ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች የመከላከያ ዘዴዎች፣ አባለዘር በሽታዎች ምንነት፣ ምጣኔ-ምግብ፣ የጡት ማጥባት ጠቀሜታ፣ የሕጻናት አመጋገብ፣ ድህረ-ወሊድና ቅድመ-ወሊድ ጥንቃቄ፣ የሕጻናት ክትባት ጥቅም፣ የግልና አካባቢ ንጽህና እንዲሁም ጥበቃ፣ በኤች.አይ.ቪና በሌሎች በርካታ የጤና ችግሮች ላይ ቀጣይነት ያለው የማህበረሰብ ውይይት እንዲካሄድ ተደርጓል፤

## በተለያዩ ቦታዎች የተከናወኑ ዋና ዋና የልማት ተግባራት ጥቅል መረጃ

| ዘርፍ | የድጋፍ ዓይነት/ግንባታ | የሚገኝበት ቦታ/ወረዳ/ | የሚገኝበት ቦታ/ቀበሌ/ | የተሰራበት ዓመት |
|---|---|---|---|---|
| | የት/ቤት ግንባታ | ኪ/ዲዳዬ | ሀላሌ | 2002 |
| | >> | ኪ/ኮይሻ | ጉሩሞ አሴ | 2003 |
| | >> | ዳሞት ሶሬ | ዶጌ ላሮሶ | 2002 |
| | >> | ኦፋ | ኦሜ ቦሎላ | 2004 |
| | >> | >> | ገሱባ ከተማ | 2005 |

| ዘርፍ | የድጋፍ ዓይነት/ግንባታ | የሚገኝበት ቦታ/ወረዳ/ | የሚገኝበት ቦታ/ቀበሌ/ | የተሰራበት ዓመት |
|---|---|---|---|---|
| ትምህርት | >> | >> | ሙሬ | 2006 |
| | >> | >> | ኮዶ | 2007 |
| | >> | >> | ዳቃያ | 2008 |
| | >> | >> | ቡሻ/ገሱባ | 2009 |
| | የፈርንቸር ድጋፍ | ዳሞት ሶሬ | ጉኑኖ | 2007 |
| | >> | ቦሎሶ ቦምቤ | ቦምቤ ከተማ | 2008 |
| | የት/ቤት ግንባታ | ቦሎሶ ሶሬ | ዩካራ | 2005 |
| | የት/ቤት ጥገና | አረካ ከተማ | አረካ | 2002 |
| | የፈርንቸር ድጋፍ | አረካ ከተማ | አረካ ፋና | 2004 |
| | የት/ቤት ግንባታ | ሶዶ ዙሪያ | በቅሎ ሰኞ | 2002 |
| | >> | >> | ሾላ ኮዶ | 2003 |
| | >> | >> | ቁጦ ሶርፔላ | 2004 |
| | >> | ሶዶ ከተማ | ሶዶ | 2005 |
| | የፈርንቸር ድጋፍ | ሶዶ ከተማ | ሶዶ | 2006 |
| | የት/ቤት ግንባታ | >> | ሶዶ | 2007 |
| | የህዝብ ቤተመጻህፍት ግንባታ | >> | >> | 2003 |
| | የት/ቤት ግንባታ | ዳሞት ጋሌ | አቤ ጃጌ | 2003 |
| | የት/ቤት ዕድሳት | ዳሞት ጋሌ | ሀርቶ ቡርቅቶ | 2002 |
| | የመምህራን መኖሪያ ግንባታ | >> | >> | 2002 |
| | የት/ቤት ግንባታ | ዳሞት ፑላሳ | ዋርቢራ ሱቄ | 2003 |
| | >> | ዳሞት ወይዴ | ቶራ ዉሊሾ | 2009 |
| | >> | ቦዲቲ ከተማ | ቦዲቲ ሁለተኛ ደረጃ | 2002 |
| | >> | >> | >> መ/ደረጃ | 2001 |
| | >> | ድጉና ፋንጎ | ቢጣና | 2009 |
| | >> | >> | ኤዶ ድጉና | 2004 |
| | >> | ሁምቦ ጠበላ | ሁምቦ ጠበላ | 2001 |
| | የመምህራን መኖሪያ ቤት ግንባታ | ሁምቦ | አንካ ወቻ | 2003 |
| | የመምህራን መኖሪያ ቤት ግንባታ | >> | አበላ ጋፋታ | 2004 |
| ጤና | የጤና ኬላ ግንባታ | ኪንዶ ዲዳዬ | ዘሬዳ | 2oo4 |
| | >> | ኪ/ኮይሻ | ሙንዴና | 2002 |
| | >> | ቦሎሶ ሶሬ | ባዳዬ | 2004 |
| | >> | >> | አፋማ ሚኖ | 2002 |
| | >> | ድጉና ፋንጎ | ቢላቴ ኤታ | 2002 |

Wolaytta Worqaa Mayzzana!

| ዘርፍ | የድጋፍ ዓይነት/ግንባታ | የሚገኝበት ቦታ/ወረዳ/ | የሚገኝበት ቦታ/ቀበሌ/ | የተሰራበት ዓመት |
|---|---|---|---|---|
| | >> | >> | ፋንጎ በሎሶ | 2002 |
| | >> | ሁምቦ | ጮካሬ | 2002 |
| አካባቢ ጥበቃ | ደን ተከላ | ሶዶ ዙሪያ | ቡጌ ዋንቼ | 2007-10 |
| | የዘር ብዘት ማዕከል ማቋቋም | ሁምቦ | አምፖ ኮይሻ | 2009-10 |
| | ደን ተከላ | ኦፋ | ዋጭጋ ኤሾ፣ ማቻ ጎጋራ፣ ኮዶ እና ምሺ አልዳዳ | 2010 |
| | የመስኖ ቦይ ጥገና | >> | ደቃያ | 2010 |
| | የንጹህ መጠጥ ውሃ ግንባታ | ኪ/ኮይሻ | ሙንዴና | 2003 |
| | >> | ቦ/ቦምቤ | ጊዶ ማጣላ | 2010 |
| | ንጹህ የመጠጥ ውሃ ግንባታና ጀነሬተር | አረካ ከተማ | አረካ ከተማ | 2009 |
| የንጹህ መጠጥ ውሃ ስራ | የንጹህ መጠጥ ውሃ ግንባታ | ዳ/ጋሌ | ዳ/ሞኮኒሳ | 2010 |
| | >> | ዳ/ወይዴ | በዴሳ | 2010 |
| | >> | ድጉና ፋንጎ | ቢላቴ ኤታ | 2003 |
| | >> | ሁምቦ | አበላ ማራቃ | 2010 |
| | ምንጭ ማጎልበት | ኦፋ | ዋጭጋ ኤሾ፣ ኮዶ እና ምሺ አልዳዳ | 2010 |
| ለአቅመ ደካሞች ድጋፍ እና እንክብካቤ | መኖሪያ ቤት ግንባታ | ሶዶ | ሶዶ | 2003-04 |
| | የተሃድሶ አገልግሎት | ሁምቦ | | 2009 |
| | የመኖሪያ ቤት ግንባታ | >> | አባያ ጉሩቾ | 2004 |
| ከተማ ልማት | የአስፓልት መንገድ ግንባታ | ሶዶ ከተማ | ሶዶ ከተማ | 2009 |
| ምግብ ዋስትና | የንብ ማነብ ስራ | ኦፋ | ምሺ ምቻ፣ ዳቃያ፣ ዋጭጋ ኤሾና ኮዶ | 2010 |
| | የአፕል ምርት ስራ | ኦፋ | ምሺ አልዳዳ፣ አሜ በሎላ፣ ዛሞና አፋ ሄራሞ | 2010 |

## ባለፉት 18 ዓመታት ወላይታ ልማት ማህበራችንን በቦርድ ሰብሳቢነት ያገለገሉ ግለሰቦች

| ተ.ቁ | የሰብሳቢው ስም | ያገለገሉበት ዓመት (እ.አ.አ) |
|---|---|---|
| 1 | ዶ/ር ቀለሙ ደስታ | 2000- 2002 |
| 2 | አቶ አብርሃም ባቾሬ | 2003- 2009 |
| 3 | ዶ/ር ኤልያስ ኡራጌ | 2010- 2011 |
| 4 | አቶ መለሰ መና | 2012- 2013 |
| 5 | አቶ ታምራት ሞታ | 2013- 2016 |
| 6 | አቶ አማኑኤል አብርሃም | 2016 -እስከ አሁን |

## ባለፉት 18 ዓመታት ማህበራችንን በዋና ዳይሬክተርነት ያገለገሉ ግለሰቦች

| ተ.ቁ | የዋና ዳይሬክተሩ ስም | ያገለገሉበት ዓመት (እ.አ.አ) |
|---|---|---|
| 1 | አቶ አልታዬ አየለ | 2000 - ማርች 2018 |
| 2 | አቶ ፍሬው ሞገስ | ኤፕሪል 2018 - ኦክቶበር 2018 |
| 3 | አቶ ሀብታሙ ጢሞቲዎስ | ኖቬምበር 2018 - እስከሁን |

D.C.C
ዳሞታ ኮንስትራክሽን ኩባንያ

# 1. በትኩረት አቅጣጫዎች

## 1.1 የሰው ሀብት ልማት (Human Capital Development)


### ◇ የትምህርት ጥራትና ተደራሽነት

የወላይታ ልማት ማህበር የአካባቢውን ህዝብ የልማት ፍላጎት ለማርካትና ከድህነትና ኋላ ቀርነት የተላቀቀችን ወላይታን የማየት ራዕዩን ለማሳካት ከያዛቸው ሶስት አበይት የትኩረት አቅጣጫዎች አንዱ ሆኖ ልማት ማህበሩ በዚህ የትኩረት አቅጣጫ በተገባደደው የአውሮፓውያን ዓመት በትምህርት ጥራትና ተደራሽነት እንዲሁም በአቅም ግንባታ ስልጠና ዘርፍ በርካታ ተግባራትን አከናውኗል፤ የወላይታ ሊቃ ት/ቤት፣ የተፋጠነ ትምህርት ፕሮጀክትና ልማት ማህበሩ በውስጥ የበጀት ዓቅሙ የሚሰራቸው የትምህርትና ስልጠና ተግባራት እንደሚከተለው ተቃኝተዋል።

### 1.1.1 ወላይታ ሊቃ ትምህርት ቤት


ወላይታ ሊቃ ት/ቤት ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ በምህንድስና፣ በጤና መኮንንነት፣ በሌሎች የጤና ትምህርት ዘርፎች እና በኮምፒዉተር ሳይንስ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት 432 ተማሪዎችን በከፍተኛ ውጤት ስኬታማ ት/ቤት ሲሆን የት/ቤቱ 69 ከመቶ ማለትም 298 ተማሪዎች የሚገኙት በህክምና ዶክቴሬት ድግሪ ትምህርት ዘርፍ ነው። ከእነዚህ ተማሪዎች መካከል ከሚቀጥለው ዓመት ጀምሮ በተከታታይ 40 ያህል የሕክምና ዶክተሮች በየዓመቱ መመረቅ ይጀምራሉ፤ በዚህ ት/ቤት እ.አ.አ በ2018 በጀት ዓመት የሚከተሉት ዋና ዋና ተግባራት ተከናውነዋል።

- ◇ 356 ልማት ማህበሩ ስፖንሰር ያደረጋቸው ተማሪዎች የመኝታ፣ የምግብ፣ የትምህርት መሳሪያዎች፣ የትራንስፖርት፣ የንጽህና፣ የኪስ ገንዘብና ሌሎች አስፈላጊ መሳሪያዎች አቅርቦትና ድጋፍ ተሰጥቷል፤
- ◇ ከ3 ሚሊዮን ብር በላይ የሆነ ዘመናዊ የቤተ ሙከራ መሳሪያዎች ከስቴም ሲኔርጂ ጋር በመተባበር እንዲገጠሙና አገልግሎት ላይ እንዲውሉ ተደርጓል፤



በስቴም ሲኔርጂ ከተበረከቱ የቤተሙከራ መሳሪያዎች በከፊል

- ◇ 904 የቡድን ስራዎች፣ 289 የፕሮጀክት ስራዎች፣ 387 የማጠቃለያ ፈተናዎች እና 53 ሞዴል ፈተናዎች ተሰጥተዋል፤ ለሴት ተማሪዎች፣ ዝቅተኛ ውጤት ላስመዘገቡ ተማሪዎች እና ብሄራዊ እና ክልላዊ ፈተና ተፈታኝ ተማሪዎች የቱቶሪያል ትምህርት ተሰጥቷል፤
- ◇ 39 የኤሌክትሮኒክ ትምህርት ክፍለ ጊዜዎች (e-classes) ተግባራዊ ተደርጓል፤
- ◇ የመማር ማስተማር ሂደትን ለማሻሻል 78 የውስጥ ግምገማዎች ተደርገዋል፤
- ◇ በት/ቤቱ የሳይንስ ትምህርቶች ላይ የቤተሙከራ ክፍለ ጊዜዎችን ከቀድሞው በተሻለ በመጠቀም የተግባር ትምህርትን አጠናክሯል፤
- ◇ በት/ቤቱ የተለያዩ አደረጃጀቶችን ማለትም የዲፓርትመንት፣ ስኳድ፣ የተማሪዎች ፓርላማ፣ ወላጅ መምህርና ተማሪዎች ህብረት በመጠቀም የመማር ማስተማር ስራ እንዲጠናከር ተደርጓል፤
- ◇ 356 በልማት ማህበሩ ለሚደገፉ ተማሪዎች የምግብ አገልግሎት ተሰጥቷል፣
- ◇ ተማሪዎች በስነልቦና ዝግጁ እንዲሆኑ በስነልቦና ባለሙያ የምክር አገልግሎት ተሰጥቷል፤



የወ/ሊቃ/ት/ቤት ተማሪዎች በት/ት ገበታቸው



የወ/ሊቃ/ት/ቤት 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ሽኝት መርሃግብር

## የ2010 የተማሪዎች ውጤት

| የፈተናው ዓይነት | ውጤት | የተማሪው ብዛት | ማብራሪያ |
|---|---|---|---|
| የት/ቤቱ ፈተና | ከ95% | 80 | |
| | ከ86-95% | 203 | |
| | ከ75-85% | 166 | |
| ክልላዊ ፈተና | ከ85% በላይ | 46 | |
| | 95% እና በላይ | 8 | |
| ብሔራዊ ፈተና | በሁሉም የት/ት ዓይነቶች A | 61 | |
| | 4:00 ከB ጋር የተቀላቀለ | - | |
| | ከ4:00 በታች | - | 3.86 (ዝቅተኛ) |
| ዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተና | ከ500-599 | 66 | |
| | ከ600 በላይ | 6 | |
| | ከ500 በታች | - | |

## በ2011 ዓ.ም. በት/ቤቱ የሚገኙ ተማሪዎችን ብዛት

| የክፍል ደረጃ | በወልማ ድ ጋፍ የሚማሩ ተማሪዎች | | | ወጪ በመጋራት የሚማሩ ተማሪዎች | | | ድምር | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ | ወ | ሴ | ድ |
| 5 | 12 | 3 | 15 | 12 | 17 | 29 | 24 | 20 | 44 |
| 6 | 11 | 5 | 16 | 9 | 10 | 19 | 20 | 15 | 35 |
| 7 | 8 | 2 | 10 | 26 | 11 | 37 | 34 | 13 | 47 |
| 8 | 11 | 2 | 13 | 26 | 9 | 35 | 37 | 11 | 48 |
| **5-8** | **42** | **12** | **54** | **73** | **47** | **120** | **115** | **59** | **174** |
| 9 | 40 | 1 | 41 | 25 | 15 | 40 | 65 | 16 | 81 |
| 10 | 17 | 7 | 24 | 29 | 23 | 52 | 46 | 30 | 76 |
| 11 | 19 | 3 | 22 | 26 | 16 | 42 | 45 | 19 | 64 |
| 12 | 28 | 1 | 29 | 36 | 16 | 52 | 64 | 17 | 81 |
| **9-12** | **104** | **12** | **116** | **116** | **70** | **186** | **220** | **82** | **302** |
| **ድምር** | **146** | **24** | **170** | **189** | **117** | **306** | **335** | **141** | **476** |

### 1.1.2 የተፋጠነ ትምህርት ፕሮጀክት (Acclerated Learning for Africa Project)

**የተፋጠነ ትምህርት ፕሮጀክት (Acclerated Learning for Africa Project) ወላይታ ልማት ማህበር ከጂኒሻ ግሎባል ጋር በመተባበር የሚተገብረው ፕሮጀክት ነው። ፕሮጀክቱ ዕድሜያቸው ከ9-14 የሆኑ በድህነት ምክንያት ወደ ት/ቤት ያልገቡ ህጻናትን በመቀበል ሙሉ የትምህርት ቁሳቁሶችን በማሟላት በአንድ ዓመት ቅዳሜን ጨምሮ ከ1-3 ኛ ክፍል በማስተማር በወረዳው የትምህርት ጽ/ቤቶች በኩሉ የተዘጋጀ ማጠቃለያ ፈተና ተፈትነው ሲያልፉ ወደ 4ኛ ክፍል ተዛውረው ከእኩዮቻቸው ጋር እንዲስተካከሉ በማድረግ፣ የእነዚህን ተማሪዎች እናቶች የኢኮኖሚ አቅም ለመገንባት ከገቢያቸው የተወሰነ በማስቀጠብና ከፕሮጀክቱ መነሻ የሚሆን ገንዘብ በመስጠት፣ የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶችን አቅም በመገንባትና የህጻን ለህጻን ትምህርትን በመደገፍ የሚሰራ ፕሮጀክተ ነው። በበጀት ዓመቱ በዚህ ፕሮጀክት የተከናወኑ ተግባራት ዋና ዋና ተግባራት ቀጥሎ ተዘርዝረዋል።**

- **ለ65 (ወ-51 ሴ-14) አመቻች መምህራን የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷቸው የትምህርት አሰጣጣቸውን እንዲያሻሽሉ ተደርጓል፤ ወደ ገጽ 21 ዞሯል።**

# DAMOTA WOLAYTA FARMERE CO-OPERATIVE UNION LiMITED COMPANY

ዳሞታ የወላይታ ገበሬዎች ህብረት ሥራ
ዩኒየን ኃ.የተ.

አድራሻችን ፡- ወላይታ ሶዶ መርካቶ አተና
መሄጃ መንገድ

በስልክ ቁጥር፡-
0465510642/0927000160

ፋክስ፡- 0465512955

E-mail:meskdwfcu@gmail.com

የአዲስ አበባ አድራሻችን ሳሪስ


# አዲስ ጤና መካከለኛ ክሊኒክ

## በዶ/ር ደስታ ሴባ እና በስፔሻሊስት ሐኪሞች

- አጠቃላይ ሕኪምናና የተሟላ የላቦራቶሪ ምርመራ ከአዉሮፓ ባስመጣናቸዉ እጅግ ዘመናዊ የሕኪምና መገልገያ ማሽኖች በመታገዝ ደረጃዋን የጠበቀ ሕክምና እንሰጣለን።



- የዉስጥ ደዌ ፤ መለስተኛ ቀዶ ጥገና
- የማህጸን ሕክምናና የፅንስ ክትትል
- የህፃናት ሕክምና ከጨቅላ እስከ አዋቂ
- የቆዳና የአባላዘር በሽታ ሕክምና
- የአእምሮ ሕክምናና ምክር አገልግሎት



- በ **Digital color Doppler Ultrasound Imaging**
  - የልብ **Echocardiography**
  - **Doppler Ultrasound**
  - **Ultrasonography**



- Digital የልብ ECG ምርመራ
- CBC,BLOOD CHEMISTERY
- Serum electrolyte (Na+,K+,ca+2 ,cl-)
- Thyroid function test (T3,T4,TSH,)
- Cancer markers (PSA,Ca125,CEA,..



- የስነ-ደዌ (pathology) የካንሰር ምርመራ በስነ-ደዌ ስፔሻሊስት ሐኪም

አድራሻችን፤- ወላይታ ሶዶ መርካቶ ከገበያ አዳራሽ ፊት ለፊት
**0461800930/0911826398**

# የታታሪነትና የማያቋርጥ ቅንጅታዊ ጥረት ውጤት

ትምህርት የልማት ሁሉ መሰረት ነው! በትምህርት የሚገኝ ዕውቀት ሀገርን ለመገንባት ያስችላል። ሳይንሳዊ ዕውቀት ለችግሮች ሁሉ መፍቻ ቁልፍ ነው። የሀገራችን የኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ችግሮች ዋናው መንስኤ የዕውቀት ማነስና የድንቁርና ችግር ነው።

ወላይታ ልማት ማህበር የዕውቀትን ጥቅም በመረዳት በሰው ሀብት ልማት ላይ መስራት ከጀመረ ሰነባብቷል። በ2ኛው ሚሌኒየም መባቻ ላይ የወላይታ ሊቃ ትምህርት ቤትን በማቋቋም በአካባቢው ያለውን የተማረ የሰው ሀይል እጥረት ለመቅረፍ ብሎም ሀገሪቱን ለማሳደግ ሰንቆ በተነሳው ራዕይ ከፍተኛ ውጤት ማስመዝገቡንም ቀጥሏል። የወላይታ ሊቃ ት/ቤት ብሩህ አዕምሮ ያላቸውን ተማሪዎች አወዳድሮ በመቀበል የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግቡ በማስቻል በዞኑ ብቃት ያለው የሰው ሃብት በማልማት የራሱን ድርሻ እያበረከተ ይገኛል።

ት/ቤቱ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በክልላዊ፣ ብሔራዊ እና ዩኒቨርሲቲ መግቢያ ፈተናዎች እጅግ ከፍተኛ የሚባል ውጤት እያስመዘገበ ነው። ይህ ውጤት ደግሞ የልማት ማህበሩ፣ የት/ቤቱ እና የተማሪዎች ቅንጅታዊ ታታሪነትና የማያቋርጥ ጥረት የስራ ውጤት መሆኑ እሙን ነው። በት/ቤቱ ስላለው የመማር ማስተማር ጥንካሬ ከአንድ የት/ቤቱ ተማሪ ጋር ያደረግነውን ቆይታ እናቀርብላችኋለን ተከታተሉን። መልካም ቆይታ!

ወልማ፡ ስምህን እና ተወልደህ ያደግክበትን ብትነግረን...

በረከት፡ ስሜ በረከት ፖሊሱ ይባላል። ተወልጄ ያደግሁት በኪንዶ ኮይሻ ወረዳ በሌ ከተማ ነው።

ወልማ- ወደ ወላይታ ሊቃ ት/ቤት እንዴት መግባት ቻልህ?

በረከት፡ ወደ ወላይታ ሊቃ ት/ቤት የገባሁት በ2008 ዓ.ም የስምንተኛ ክፍል ክልላዊ ፈተና ተፈትኜ እያለሁ የወላይታ ሊቃ ት/ቤት ተማሪዎችን ለመቀበል ያወጣውን ማስታወቂያ ተመልክቼ ተመዘገብኩ፣ ት/ቤቱ ያዘጋጀውን የመግቢያ ፈተና ተፈትኜ በጥሩ ውጤት አልፌ ነው የተቀላቀልኩት።

ወልማ፡ አሁን ስንተኛ ክፍል ነህ የክፍል ውጤትህስ ምን ያህል ነው?

በረከት፡ አሁን 11ኛ ክፍል ነኝ፣ በ11ኛ ክፍል የመጀመሪያ ሴሚስቴር ውጤቴ 98.3% ነው።


ተማሪ በረከት ፖሊሱ


ወልማ፡ ቀድሞ የነበርክበት ት/ቤትና ወላይታ ሊቃ ልዩነታቸው ምንድን ነው?

በረከት፡ እጅግ ብዙ ልዩነት አለ፣ እዛ ጊዜዬን በትክክል አልጠቀምም፣ መምህራኑም ቢሆኑ የት/ት ክፍለ ጊዜ አሟጠው አይጠቀሙም፣ በት/ቤቱ ያሉትም ነገሮች ሙሉ የሚባሉ አይደሉም።

እዚህ ግን ያለኝን ጊዜ በአግባቡ ለት/ት እጠቀማለሁ፣ መምህራኑ በቂ ዝግጅት በማድረግ ያስተምራሉ፣ በት/ቤቱ በቂ የቤተመጽሐፍትና ቤተሙከራ አገልግሎቶች ስላሉ ሳልቸገር እማራለሁ። በት/ቤቱ ያለው ሁኔታም ለመማር በጣም ምቹ ነው፣ ከዚህም የተነሳ አመለካከቴ ሁሉ ተቀይሯል፣ ይህም በ10ኛ ክፍል ከፍተኛ ውጤት (4:00) እንዳስመዘግብ አስችሎኛል፣ከዛ ከመጣሁ በኋላ በትምህርቴ ከፍተኛ ለውጥ አምጥቻለሁ፣ አሻሽያለሁ። እግ/ር ቢፈቅድ የ12ኛ ክፍል ውጤቴም ጥሩ ይሆናል።

ወልማ፡ ለአንባቢያን እና ለአጠቃላይ ህብረተሰብ የምታስተላልፈው መልዕክት ካለህ...

በረከት- እኔ በተለይም ለተማሪዎች የማስተላልፈው መልዕክት ሁላችሁም እንደእኔ ወደ ወላይታ ሊቃ ት/ቤት ለመግባት በርትታችሁ አጥኑ ነው የሚለው። ሌላው መልዕክቴ ከውጭ ያለው የህብረተሰብ ክፍል ለት/ቤቱ ያለው አመለካከት ጥሩ አይደለም፣ ት/ቤቱ ፍትሃዊነት የለውም ስለሚባል በት/ቤቱ ምንም ዓይነት ፍትሃዊነት የሌለው ስራ እንደማይሰራ እና ህብረተሰቡ ይህንን የተሳሳተ አመለካከት ቢያስወግድ እላለሁ። በት/ቤቱ የሚመጣው የላቀ ውጤት በጠንካራ ስራ የሚመጣ ነው። የትምህርት ቤቱ አስተዳደር ጠንክሮ ነው የሚሰራው፣ የት/ቤቱ መምህራን ጠንክረው ይሰራሉ፣ ተማሪዎች ጠንክረው ይሰራሉ። ሚስጢሩ ይሄና ይሄ ብቻ ነው።




አመቻች መምህራን በስልጠና ላይ

- የተፋጠነ ትምህርት ፕሮጀክት የሚተገበርባቸው ት/ቤት መምህራን፣ ርዕሳነ መምህራን፣ የወረዳ ት/ቤቶች ጽ/ቤት ሃላፊዎችና ሱፐርቫይዘሮች የሁለት ቀናት የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፤
- ለ1050 የቅድመ መደበኛ ክፍል ተማሪዎች 262 ደርዘን ደብተር፣ 1050 እርሳስና 126 የፊደል ገበታ ተበርክቷል፤
- ለ1625 በተፋጠነ ትምህርት ፕሮጀክት ለታቀፉ ተማሪዎች ደብተር፣ አስክሪቢቶና አርሳስ አሟልቶ አስተምሯል፤
- ለዋርቢራ ጎሎ ት/ቤት የሶስት መማሪያ ክፍሎች ወለል ግንባታ ተካሂዷል፤
- 158 የተማሪ መቀመጫ ዴስኮች፣ 3 ጥቁር ሰሌዳዎችና 325 ትንንሽ ጥቁር ሰሌዳዎች ፕሮጀክቱ



ለተማሪዎች ከተበረከቱ የትምህርት ቁሳቁሶች በከፊል

- ለ1609 (ወ-984 ሴ-625) ተማሪዎች የብቃት መመዘኛ ፈተና ተሰጥቷቸው ወደ 4ኛ ክፍል ተዛውረዋል፤
- 65 የመንደር ቁጠባና ብድር ማህበራትን በማቋቋም ለሁሉም ማህበራት የቁጠባ ሳጥን በማበርከት ከብር 53 ሺ.ህ በላይ ብር እንዲቆጥቡ አድርጓል ፤
- በ2017 እ.ኤ.አ. ለተደራጁ 60 የራስ አገዝ ቡድኖች በቆጠቡት ገንዘብ ላይ ተጨማሪ ሁለተኛ ዙር ከፕሮጀክቱ መነሻ ካፒታል የሚሆን ብር 290,250 (ሁለት መቶ ዘጠና ሺ.ህ ሁለት መቶ ሃምሳ ብር) ተሰራጭቷል፤
- ለ30 የተፋጠነ ትምህርት ፕሮጀክት አመቻች መምህራን በአጠቃላይ ተግባር ተኮር የመማር ማስተማር ስነዘዴና በሌሎች ተያያዥ ርዕሰ ጉዳዮች ለአስር ቀናት ስልጠና ተሰጥቷል፤
- ዕድሜያቸው ከ9-14 የሆነ ወደ ትምህርት ቤት ያልሄዱ 900 (ወ-467 ሴ-433) ወላጅ አጥና የደሃ ደሃ የሆኑ ተማሪዎች ከዳሞት ሶሬ ወረዳ አስር ቀበሌዎች ተመዝግበው በፕሮጀክቱ ሙሉ የትምህርት ቁሳቁስ (በሁለት ዙር 600 ደርዘን ደብተር፣ 36 ፓኬት እስክሪቢቶና 900 እርሳስ) ተሟልቶላቸው

በትምህርት ገበታ ላይ ይገኛሉ፤በፕሮጀክት ለታቀፉ ትምህርት ቤቶች የትምህርት ግብዓቶች ድጋፍ ተደርጓል፤

- 21 ፕሮጀክቱ ለሚተገበርባቸው ት/ቤቶች 1155 የአንደኛ ደረጃ አማርኛ፣ እንግሊዝኛና አካባቢ ሳይንስ ማጣቀሻ መጽሃፍት ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፤




ተማሪዎች በመስክ ትምህርት ላይ

- 59 የተማሪ መቀመጫ ዴስኮች ድግፍ በዳሞት ሶሬ ወረዳ ለሚገኙ ጉኑኖ ሐሙስ፣ ዛሚኔ ኮልባዬና ሶሬ ማሺዶ ት/ቤቶች ተደርጓል፤
- በዳሞት ሶሬ ወረዳ የተፋጠነ ትምህርት ፕሮጀክቱ በሚተገበርባቸው አስር ቀበሌዎች 30 የራስ አገዛ ማህበራት ተመስርተው ከገቢያቸው በቁጠባ እንዲሰማሩ ተደርጓል፤

ወላይታ ልማት ማህበር የሚያከናውናቸውን የልማት ተግባራት በተለይም በሶስቱ የትኩረት አቅጣጫዎች ከአጋር ድርጅቶችና በአባላት መዋጮ ጋር የተለያዩ ተግባራትን ያከናውናል፤ ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ተግባራት ማህበሩ በራሱ የውስጥ አቅም በሰው ሃብት ልማት ዘርፍ ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት ናቸው፡፡

- ለ100 (ወ-57 ሴ-43) ደሃ እና ወላጅ አጥ ለሆኑ ተማሪዎች በብር 16970 (አስራ ስድስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ሰባ ብር) የትምህርት ቁሳቁስ ድጋፍ ተደርጓል፤
- ለ349 (ወ-303 ሴ-46) ከወላይታ ዞን ሁሉም አካባቢዎችና ከዞኑ ውጭ ከሚገኙ የወልማ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ለተመለመሉ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ትምህርታቸውን ለሚገፉ ተማሪዎች ወደ ዩኒቨርሲቲ ሲሄዱ እና ሲመለሱ ከብር 297 ሺህ በላይ ድጋፍ አድርጓል፤
- በሶዶ ዙሪያ ወረዳ ቶሜ ጌሬራ ት/ቤት ሁለት የመማሪያ ክፍሎች ጥገና ተደርጓል፤ የዝናብ ዉሃ ለማጠራቀም ሁለት ባለ 10000 ሊትር የውሃ ማጠራቀሚያ ተገዝቶ ተገጥሟል፤



የቶሜ ጌሬራ ት/ቤት ክፊል ገጽታ

- በሶዶ ዙሪያ ወረዳ ዋራዛ ላሾ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት በህብረተሰቡ ተጀምረው የነበሩ አንድ ላይብራሪ፣ ስምንት የአስተዳደር እና አራት መማሪያ ክፍሎች ያላቸው ባለ ሁለት ብሎክ ህንጻዎችን አስፈላጊ ግብዓቶችን በማሟላት አጠናቅቆ ለአገልግሎት አብቅቷል፤
- ከ298 ሺህ ብር በላይ ወጪ በማድረግ በዞኑ ውስጥ ለሚገኙ ሁለተኛ ደረጀ ት/ቤቶች የ170 የተማሪ ዴስክ ድጋፍ አድርጓል፤



የተማሪዎች መቀመጫ ድጋፍ

- ለወላይታ ሊቃ ት/ቤት ከብር 460 ሺህ በላይ ወጪ በማድረግ 120 ጠረጴዛዎችንና 240 ወንበሮችን አሰርቶ አበርክቷል፤
- 100 % ለት/ቤቶች ስርዓት የሚገዙና በስነ ምግባራቸው የታነፁ ተማሪዎችን ማፍራትን ዓላማው በማድረግ በዞኑ ውስጥ ለሚገኙ 11 ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የተማሪዎች መተዳደሪያ ደንብ ተዘጋጅቶ ተሰራጭቷል፤
- ከወላይታ ዞን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ዩኒት ከሚገኝባቸው ክላስተር አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለተወጣጡ 24 መምህራን የልዩ ፍላጎት ትምህርት ስልጠና ተሰጥቷል፤30 የ1ኛ እና 2ኛ ክፍል የምልክት ቋንቋ የተማሪ መማሪያ መጻህፍት ለ11 የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ተበርክተዋል፤

## 2. በዘላቂ የኑሮ ማሻሻያ (Sustainable Livelihood Security)

የወላይታ ልማት ማህበር የአካባቢውን ህብረተሰብ ኑሮ ለማሻሻል ከአባላትና ከለጋሽ ድርጅቶች በሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ በዞኑ ውስጥ በሚገኙ በተለያዩ አካባቢዎች አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርጉ ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፤ እያከናወነም ይገኛል።


ልማት ማህበሩ እ.ኤ.አ በ2018 በጀት ዓመት ለአርሶ አደሮች ምርጥና የተሻሻሉ የጓሮ አትክልትና ፍራፍሬ ችግኞችን በማቅረብ፣ የእርሻ መሳሪያዎችን ድጋፍ በመስጠት፣ ዘመናዊ የሐር ትል አመራረትና ንብ ማነብ ስልጠና በመስጠት፣ ዘመናዊ የንብ ቀፎ በማበርከት፣ ለህብረት ስራ ማህበራት ከ5ሚሊዮን ብር በላይ ተዘዋዋሪ ብድር ያለወለድ በመስጠትና በሌሎችም ዘርፎ ብዙ መስኮች አያሌዎችን ተጠቃሚ ሲያደርግ ከርሟል፤ ቀጥሎ ልማት ማህበሩ በዚህ በሁለተኛው የትኩረት አቅጣጫው በተለያዩ ፕሮጀክቶች ያከናወናቸው ተግባራት እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል።

### 2.1 የገጠር ስራ ዕድል ፈጠራ

ይህ ፕሮጀክት በወላይታ ዞን በተመረጡ 5 ወረዳዎች(ድገና ፋንጎ፣ ቦሎሶ ቦምቤ፣ ኦፋ፣ ኪንዶ ዲዳዬና ኪንዶ ኮይሻ) ለአርሶ አደሮች በዘመናዊ ግብርና አመራረት ዘዴ ስልጠና በመስጠት፣ የፍራፍሬ ችግኞችና አትክልት ዘሮችን ፣ ዘመናዊ የሐር ትል አመራረትና ንብ ማነብ ስልጠና በመስጠት አቅማቸውን በመገንባትና የህብረት ስራ ማህበራትን በማጠናከር አርሶ አደሮች አካባቢያቸውን ለቅቀው ለህገወጥ እንዳይዳረጉ ይሰራል። በበጀት ዓመቱ በፕሮጀክቱ የተከናወኑ ተግባራት:-


- ፕሮጀክቱ ከሚተገበርባቸው ድጉና ፋንጎ፣ ኦፋ፣ ኪንዶ ኮይሻ፣ ኪንዶ ዲዳዬ እናቦሎሶ ቦምቤ ወረዳዎች ለተወጣጡ 300 የህብረት ስራ ማህበራት አደራጆችና ስራ ፈጠራ ባለሙያዎች፣ የወላይታ ዞን ግብርና መምሪያ ሱፐርቫይዘሮችና አምስት የወልማ ሰራተኞች የህብረት ስራ ማህበራት ልማት የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፤
- የወልማ ባለሞያዎችን ጨምሮ ከ5 ወረዳዎች እና ከወላይታ ዞን ግብርና መምሪያ ለተወጣጡ 28 ባለሙያዎችና ሱፐርቫይዘሮች የግብርና ልማት የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፤
- ፕሮጀክቱ በሚተገበርባቸው ሁሉም ወረዳዎችና በተዋረድ በየቀበሌዎች ዘመናዊ የንብ ማነብ፣ የህብረት ስራ ማህበራት ልማትና የግብርና ልማት የተግባርና ንድፈ ሀሳብ ስልጠናዎች ተሰጥተዋል፤
- ለሶስት የህብረት ስራ ማህበራት ዘመናዊ የሐር ትል አመራረት በንድፈ ሀሳብና በተግባር ተሰጥቷል፤

- በህዝብ አስተዳደርና አካባቢ ልማት ለ22 (ወ-21 ሴ-1) ተሳታፊዎች የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቷል፤
- በህዝብ አስተዳደርና አካባቢ ልማት ከፕሮጀክቱ ወረዳዎች ለተወጣጡ 300 (ወ-290 ሴ-10) ተሳታፊዎች በተዋረድ ስልጠና ተሰጥቷል፤
- በፕሮጀክቱ በታቀፉ ሁሉም ወረዳዎች ለሚገኙ አርሶ አደሮች ከ100 ኪ/ግ በላይ የቲማቲም፣ ጥቅል ጎመን እና ካሮት ዘር ተሰራጭቷል።
- ከ250 ኪ/ግ በላይ ሽንኩርትና ቀይስር 4000 ከአፕል ጋር የተዳቀሉ ማንጎና 1570 ከማንጎ ጋር የተዳቀሉ አቡካዶ ችግኞች ተገዝተው ለአርሶ አደሮች ተሰራጭተዋል፤




በፕሮጀክቱ የተሰራጩ የተለያዩ የተዳቀሉ ችግኞች በማሳ ላይ

- የግብርና ማስተማሪያ ማኗል በማዘጋጀት 386 ቅጂዎችን ለፕሮጀክቱ ወረዳዎች እንዲሰራጩ ተደርጓል፤
- ምርትና ምርታማነትን ለማሻሻል የእርሻ መሳሪያዎችን (ሲፎን፣ አካፋ፣ ዘቢያ፣በእጅ የሚገፋ ጋሪ፣ ፎርካ፣ዉሃ ማጠጫ) እንዲሁም ኬሚካሎችን በመግዛት ለአርሶ አደሮች ተሰራጭቷል፤




በፕሮጀክቱ ከተበረከቱ መሳሪያዎች በእጅ የሚገፋ ጋሪና የሐር ትል መመገቢያ ፍሬም

- የሐር ትል አመራረት ስልጠና ማኗል በማዘጋጀት ለአርሶ አደሮች ማስተማሪያነት እንዲሆን ለአምራቾች ተሰራጭቷል፤
- 270 የሐር ትል መመገቢያ ፍሬም ተገዝቶ ለአምራቾች ተበርክቷል፤
- የተዘዋዋሪ ፈንድ ማስተማሪያ ማኗል በማዘጋጀት 90 ቅጂዎችን ለፕሮጀክቱ ወረዳዎች እንዲሰራጩ ተደርጓል፤ ከወላይታ ዞን ለተወጣጡ 17 የህብረት ስራ ማህበራት አመራሮች የተዘዋዋሪ ፈንድ ስልጠና ተሰጥቷል፤
- ፕሮጀክቱ ለሚተገበርባቸው ወረዳዎች 300 የጀርመንና ኬንያ ሞዴል ንብ ቀፎዎችን ማሰራት አበርክቷል፤



ለአርሶ አደሮች ከተሰራጩ ዘመናዊ የንብ ቀፎዎች በከፊል

◇ ከወላይታ ዞን ለተወጣጡ 17 ህብረት ስራ ማህበራት ከ5 ሚሊዮን ብር በላይ ተዘዋዋሪ ብድር ተሰጥቷል፤



የተዘዋዋሪ ብድር አሰጣጥ ፊርማ ስነስርዓት

## 2.2 የገጠር ምቹ ሁኔታዎችን ለዘላቂ ግብርና

ይህ ፕሮጀክት ልማት ማህበሩ ከእንግሊዝ መንግስት (UK aid) ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ በሶዶ ዙሪያ፣ ሁምቦና ኦፋ ወረዳዎች ገጠራማ አካባቢዎች የሚገኙ ምቹ ሁኔታዎችን ለዘላቂ ግብርና እንዴት ማዋል እንደሚቻል በንድፈ ሃሳብና በተግባር የሚከናወን የዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮጀክት ነው፡፡ በፕሮጀክቱ ምርትና ምርታማነት ማሻሻል የሚያስችሉ የጓሮ አትክልቶችና ፍራፍሬ አመራረት ዘመናዊ ስልጠና በመስጠት፣ ምርጥ ዘሮችን ለአርሶ አደሩ በማበርከት፣ የመንደር ብድርና ቁጠባ ማህበራትን በማጠናከርና በመከታተል እንዲሁም የህብረት ስራ ማህበራትን በማጠናከር ትኩረቱን በማድረግ የሚሰራ ሲሆን በፕሮጀክቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራትን እንመልከታቸው፡፡

◇ የአፈር ለምነትን ለመጨመር የተፈጥሮ ማዳበሪያ (ኮምፖስት) አዘገጃጀት በአርሶ አደሮች ጓሮና በሌሎች ቦታዎች ለማሳያነት ተሰርቷል፤ በዚህም አርሶ አደሮች የኮምፖስት አዘገጃጀት ተለማምደዋል፤


◇ የ2018 ዓለም አቀፍ የአየር ንብረት ቀን ሲከበር (ጁን 5) በአካባቢ ጥበቃ ዙሪያ የህብረተሰብ ማነቃቂያ ተደርጓል፤

◇ በሶዶ ዙሪያ፣ ሁምቦ እና ኦፋ ወረዳዎች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ፕሮጀክቱ ባቋቋመቸው 75 የተማሪዎች ክበባት አማካይነት ስለጓሮ አትክልት አመራረት ትምህርት ተሰጥቷል፤


◇ ለሶስት ት/ቤቶች ባለ 5,000 ሊትር  ውሃ ማጠራቀሚያ ተሰጥቶ ውሃ በመያዝ  በበጋ ወራት አትክልቶችን ማምረት እንዲችሉ ተደርጓል፤

◇ በሶዶ ዙሪያ፣ ሁምቦና ኦፋ ወረዳዎች ለሚገኙና በፕሮጀክቱ በታቀፉ 8 ቀበሌዎች ለሚገኙ አርሶአደሮች 1,400 ከአፕል ጋር የተዳቀሉ የማንጎ  ችግኞች ተበርክተዋል፤

◇ በተለያየ ገቢ ማስገኛ ተግባራት ተደራጅተው ለተሰማሩ ሶስት የህብረት ስራ ማህበራት ለእያንዳንዳቸው ብር 100 ሺህ (በአጠቃላይ 300 ሺብር) መነሻ ካፒታል የተዘዋዋሪ ብድር ተሰጥቷቸው የገቢ አቅማቸውን እንዲያሻሽሉ ተደርጓል፤



ለሶስት ት/ቤቶች ከተሰራጩ የውሃ ማጠራቀሚያዎች የዋጭጋ ቡሻ ት/ቤት




ካሮትና ጥቅል ጎመን ማሳ ላይ

- በተለያየ ገቢ ማስገኛ ተግባራት ተደራጅተው ለተሰማሩ ሶስት የህብረት ስራ ማህበራት ለእያንዳንዳቸው ብር 100 ሺህ (በአጠቃላይ 300 ሺ.ብር) መነሻ ካፒታል የተዘዋዋሪ ብድር ተሰጥቷቸው የገቢ አቅማቸውን እንዲያሻሽሉ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል፤
- በሶዶ ዙሪያ፣ ሁምቦና ኦፋ ወረዳዎች ለሚገኙና በፕሮጀክቱ በታቀፉ 8 ቀበሌዎች ለሚገኙ አርሶአደሮች 1,400 ከአፕል ጋር የተዳቀሉ የማንጎ ችግኞች ተበርክተዋል፤
- ለመንደር ቁጠባና ብድር ማህበራት በፕሮጀክቱ ድጋፍ 30 የገንዘብ ቁጠባ ሳጥኖች ተበርክቷል፤ ለተመረጡ 10 የመንደር ቁጠባና ብድር ማህበራት ለገቢ ማስገኛነት 10 በእንስሳት የሚሳቡ ጋሪዎች ተሰጥቷቸዋል፤
- ለ706 (ወ-506 ሴ-200) አርሶ አደሮች ስለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠና ተሰጥቷል፤
- ለፕሮጀክቱ ሰራተኞች ስለአየር ንብረት ለውጥ የአሰልጣኞች ስልጠና ተሰጥቶ በተዋረድ ተጠቃሚዎችን እንዲያሰለጥኑ ተደርጓል፤
- ከ30 የመንደር ቁጠባና ብድር ማህበራት የተወጣጡ 30 ሴት አርሶ አደሮች የማገዶ ቆጣቢ ምድጃ አሰራርና ጠቀሜታ የልምድ ልውውጥ አግኝተዋል፤
- ለፕሮጀክቱ ሰራተኞች ስለክላስቴር ደረጃ ማህበራት (Cluster Level Association)አመሰራረት ስልጠና ተሰጥቷል፤
- ስለስነጾታ የግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች በየጊዜው በመንደር ቁጠባና ብድር ማህበራት የቁጠበና ስብሰባ ጊዜ እንዲካሄዱ በመደረግ ግንዘቤያቸው መዳበር ችሏል፤
- ከ30 የመንደር ቁጠባና ብድር ማህበራት የተወጣጡ 30 ሴት ሞዴል አርሶ አደሮች "Send a cow" በተሰኘ ግብረ ሰናይ ድርጅት የተከናወኑ ምርጥ ተግባራትን ልምድ እንዲቀስሙ ተደርጓል፤ ለተመረጡ 60 አርሶአደሮች የፕሮጀክቱን ተግባራት እንዲያስፋፉና እንዲደግፉ ስልጠና ተሰጥቷል፤
- ለተመረጡ ሶስት የመንደር ብድርና ቁጠባ ማህበራት 3 የኬሚካል መርጫ ተገዝቶ ተበርክቷል፤ የመንደር ቁጠባና ብድር ማህበራትን እንዲደግፉ ለ24 (ወ-18 ሴ-6) የፕሮጀክቱ ሰራተኞች ስለግብይትና እሴት ትስስር ስልጠና ተሰጥቷል፤
- ለ30 የመንደር ቁጠባና ብድር ማበራት አባላት 691 (ወ-193 ሴ-498) ስለቤተሰብ አያያዝና ግንኙነት ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፤
- በ15 የፕሮጀክቱ በጎ ፈቃደኞች አማካይነት ለመንደር ቁጠባና ብድር ማህበራት ዓመቱን ሙሉ የዘላቂ ግብርና፣ ቁጠባና ገቢ ማስገኛ ተግባራት የቴክኒክ ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸዋል።

## 2.3 የስኳር ድንች ልማት


ይህ ፕሮጀክት ልማት ማህበሩ "Farm Concern Africa" ከተባለ ግብረ ሰናይ ድርጅት በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ በወላይታ ዞን ውስጥ የስኳር ድንች ምርት ለማሳደግ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ የስኳር ድንች ዘር በማቅረብ እና የገበያ ትስስር በመፍጠር አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ የሚያደርግ ሲሆን አጠቃላይ የፕሮጀክቱ ተግባራት በእሴት ትስስር (Value Chain) ላይ ያተኮሩ ናቸው፡፡ በ2018 እ.ኤ.አ. የተከናወኑ ተግባራት፡-

◇ 13,837(ወ-12712 ሴ-1125) አርሶ አደሮች የስኳር ድንች ዘር ተሰጥቷቸው ተጠቃሚ ሆነዋል፤ በ38 ቀበሌዎች 76 መንደሮች የስኳር ድንች ምርት የገበያ ትስስር እንዲያሳድጉ ተደርጓል፤6,500 (ወ-5610 ሴ- 890) አርሶ አደሮች 17,750 ኩንታል ስኳር ድንች እንዲያመርቱ ተደርጓል፤ ከዚህም 9,375 ኩንታል በመሸጥ ከብር 3.1 ሚሊዮን በላይ አግኝተዋል፤



ለገበያ የተዘጋጀ የስኳር ድንች ምርት

◇ በአምፖ ኮይሻ ባዮዳይቨርሲቲ ስልጠና ማዕከል ለሰርቶ ማሳያነት በአንድ ሄክታር ማሳ ላይ የስኳር ድንች ተተክሏል፤



ስኳር ድንች ማሳ ላይ...

◇ ከደ/ብ/ብ/ህ ክልል መንግስት ቢሮ የእርሻ ምርምር ተቋም ጋር በመተባበር የዘር ብዜት የሚያካሄዱ አርሶ አደሮች ስልጠና እንዲያገኙ ተደርጓል፤


◇ 13,870 አርሶ አደሮች በፕሮጀክቱ አማካይነት ተከታታይ ድጋፍና ክትትል ተደርጎላቸው የስኳር ድንች ምርት እንዲሻሻል ተደርጓል፤

◇ ከ38 ቀበሌዎች የተወጣጡ 38 የመንደር አመቻቾች እና 114 የአካባቢ ሽማግሌዎች የስኳር ድንች ምርትን እንዴት ማሳደግ እንደሚቻልና በገበያ ትስስር ላይ ስልጠና አግኝተዋል፤

ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ተግባራት ማህበሩ በራሱ የውስጥ አቅም በዘላቂ የኑሮ ማሻሻያ ዘርፍ ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት ናቸው፡፡


◇ በአምፖ ኮይሻ ሰርቶ ማሳያ ማዕከል የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችና ፍራፍሬዎች በቀላሉ በአነስተኛ ቦታ ማምረት የሚቻልበት የኩሽና ግብርናና መደብ አተካከል ዘዴ ስልጠና ለአርሶ አደሮች ተሰጥቷል፤

◇ በማዕከሉ ለሰርቶ ማሳያነት የደለቡ ከብቶች ለወላይታ ሊቃ ት/ቤት ተማሪዎች ፍጆታ እንዲውሉ ተመቻችቷል፤



በማዕከሉ እየደለቡ የሚገኙ በሬዎች...

- 32 አርሶ አደሮች ስለዘመናዊ ግብርና ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፤
- በአምስት ተፋሰሶች (ሆቢቻ ቦርኮሼ፣ ዋጭጋ ኤሾ፣ አበላ ሲፓ፣ ማንቻና ኮዶ) የግራቪሊያና ግራር ችግኞች በ12.5 ሄክታር የተራቆተ መሬት ላይ ተተክለዋል፤ ለመጪው የዝናብ ጊዜ የሚሆን 10 ሺህ ችግኞች ፈልተው ዝግጁ ሆነው ይገኛሉ፤



ለዝናብ ወራት እየተዘጋጀ የሚገኝ ችግኝ...

## 2.4 የሶዶ ከተማ የውስጥ ለውስጥ አስፋልት መንገድ ግንባታ

ልማት ማህበሩ ከዚህ ቀደም የከተማውን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በማሳለጥ፣ ኢንቨስትመንትን በመሳብ፣ ለበርካታ ወገኖች የሥራ ዕድል በመፍጠርና የበርካቶችን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር የቻለውን የወላይታ ሶደ ከተማ 10.7 ኪ/ሜ የውስጥ ለውስጥ የአስፋልት መንገድ መስራቱ ይታወቃል አሁንም በተመሳሳይ መልኩ ከወላይታ ሶዶ ከተማ አስተዳደርና ከዞኑ አስተዳደር ጋር በመተባበር የ10 ኪ/ሜ የውስጥ ለውስጥ አስፋልት መንገድ 44ሚሊዮን ብር ወጪ በማድረግ ከቻይናው HUNAN HUANDA ROAD AND BRIDGE CORPORATION ኮንትራክተር ጋር ውል ገብቶ እየሰራ ሲሆን አሁን 5 ኪ/ሜ ያህሉ ሙሉ በሙሉ አስፋልት የለበሰ ሲሆን በቅርቡ የግንባታ ሥራው በተያዘለት የጊዜ ገደብም ይጠናቀቃል ተብሎ ይጠበቃል።

## 3. በተቀናጀ ጤና (Integrated Health Service)

ወላይታ ልማት ማህበር ጤናማና በአካባቢው ልማት በንቃት የሚሳተፍ ህብረተሰብ ለመፍጠር ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ያከናውናል። በዚህም በርካታ ዜጎች የጤና መረጃ አስቀድሞ በማግኘት ከተላላፊና ተላላፊ ከሆኑ በሽታዎች ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን መከላከል እንዲችሉ በማድረግ፣ ስለአካል ጉዳትና አካል ጉዳተኝነት ግንዛቤያቸውን እንዲዳብር በማድረግ፣ የአዕምሮ ጤና መታወክ እና የሚጥል በሽታ ላለባቸው ወገኖቻችን ነጻ የሪፌራል ህክምና አገልግሎት በማመቻቸት፣ የእግር መቆልመምና አጥንት ችግር ያለባቸው ህጻናት በቀዶ ህክምና ሙሉ አካላቸው እንዲመለስ በማድረግ ያለምንም መሳቀቅ ከእድሜ እኩዮቻቸው ጋር እንዲውሉና እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ፣ ለዓይን ሞራ ግርዶሽና ለተያያዥ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ ወገኖችን በማሳከም የዓይን ብርሃናቸው እንዲመለስ እና ሌሎች ተግባራትን አከናውኗል። ቀጥሎ ልማት ማህበሩ እ.ኤ.አ. በ2018 በጀት ዓመት በዘርፉ ያከናወናቸው ዋና ዋና ተግባራት በሚከተለው መልኩ ተዘርዝረዋል።

## 3.1 የጤና ተግባቦት ለማህበረሰብ ባህሪ ለውጥ


ይህ ፕሮጀክት ልማት ማህበሩ "John Snow Inc." ከተሰኘ ግብረ ሰናይ ድርጅት ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ በወላይታ ዞን በሚገኙ 11 ወረዳዎች የሚያከናውነው ለህብረተሰቡ ተላላፊና ተላላፊ ስላልሆኑ በሽታዎች መከላከያ ዘዴዎችና ሌሎች የጤና መረጃዎችን የሚያደርስበት ሲሆን የሚከተሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

- በተላላፊ በሽታዎች፣ በስነምግብ፣ በህጻናት እንክብካቤ፣ በቤተሰብ ምጣኔ፣ በስነተዋልዶና ሌሎች ጉዳዮች 30,167 እናቶችን ያካተተ የማህበረሰብ ውይይቶች ተካሂዷል፤
- 87 የማህበረሰብ ውይይቶችን በማመቻቸት ህብረተሰቡ በተለያዩ ርዕሰጉዳዮች እንዲወያይ እና ግንዛቤያቸው እንዲለወጥ ብርቱ ጥረት ተደርጓል፤
- በቁጥር 211 (ወ-196 ሴ-15) ለሚሆኑ የ1ኛ ደረጃ ት/ቤቶች የጤና ክበባት ተጠሪዎችና የት/ቤት ር/መ/ራን በት/ቤቶች ጤናማ ልምዶችን እንዴት ማስፋፋት እንደሚችሉ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፤
- በዓመቱ 404 የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ጥበቃ ዩኒቶችና 473 ጤና ጣቢያዎች ድጋፍና ክትትል ተደርጎላቸዋል፤
- 294 በውሃና ሳኒቴሽን ዙሪያ የተደረጉ የማህበረሰብ ንቅናቄ ኩነቶችን ማስተባበር ተችሏል፤
- የነፍሰ ጡር እናቶችን ውይይት በማስተባበር የቤተሰብ ምጣኔ እና ስለልጆች አስተዳደግ ያላቸው ግንዛቤ እንዲዳብር ተደርጓል፤
- 328 የሃይማኖት መሪዎች በማህበራዊና ስነባህሪያዊ ለውጥ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፤

## 3.2 መሰረተ ማህበረሰብ ተሃድሶ ልማት

ይህ ፕሮጀክት ወላይታ ልማት ማህበር በጤናው ዘርፍ ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ "Christian Blind Mission" ከተሰኘ ግብረ ሰናይ ድርጅት በሚያገኘው የገንዘብ ድጋፍ በተለያዩ የዞኑ አካባቢዎች የሚያከናውነው የአካል ጉዳት ላለባቸው ወገኖች የተሃድሶ አገልግሎት የመስጠት፣ የስነ አዕምሮ ህክምናና የአካል ድጋፍ በመስጠት፣ የሪፌራል ህክምናና ሌሎች ተግባራትን የሚያከናውንበት ነው፡፡ ቀጥሎ ዋና ዋና የዓመቱ ክንውኖች ተዘርዝረዋል፡፡

- ለ222 (ወ-113 ሴ-109) የአካል ጉዳት ላለባቸው ህጻናት የቤት ለቤት ተሃድሶ አገልግሎት ተሰጥቷል፤
- 1,471 (ወ-774 ሴ-697) ግለሰቦች የህክምና (ቀዶ ጥገና፣ መድሀኒት፣ የአካል ድጋፍ) አገልግሎት አግኝተዋል፤
- 461 (ወ-244 ሴ-217) የሚጥል በሽታ ያለባቸው ግለሰቦች የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ተደርጓል፤
- ከወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ሪፌራልና ማስተማሪያ ሆስፒታል ጋር በመተባበር ለሶስት ቀናት በተደረገው የዓይን ቀዶ ህክምና ዘመቻ 949 የዓይን ችግር ላለባቸው ወገኖች የዓይን ቀዶ ህክምና ተደርጎላቸው ጥሩ ጤንነት ላይ ይገኛሉ፤



የዓይን ህክምና የተደረገላቸው ወገኖች

- ከሶዶ ክርስቲያን እና አዲስ አበባ ኪዩር ሆስፒታል ጋር በመተባበር 4 (ወ-3 ሴ-1) የእግር አጥንት ችግር ላለባቸው ወገኖች ህክምና ተሰጥቶ በጥሩ ጤንነት ላይ ይገኛሉ፤
- 4 እግራቸው ለተቆረጠባቸው ወገኖቻችን ሰው ሰራሽ እግር ተገጥሞላቸው መንቀሳቀስ ችለዋል፡፡
- 46 የተለያየ የአካል ጉዳት ላለባቸው ወገኖች 23 ክራንች፣ 25 ነጭ በትርና፣ 3 ዊልቼር ተበርክቶ ያለችግር መንቀሳቀስ ችለዋል፤
- 5 (ወ-4 ሴ-1) የእግር መቆልመም ችግር ላለባቸው ህጻናት ቀዶ ህክምና ተደርጎ በጥሩ ጤንነት ላይ ይገኛሉ፤

257 (ወ-125 ሴ-132) የተለያየ የአካል ጉዳት ያለባቸው ህጻናት የስነልቦና ምክርና የትምህርት መሳሪያዎች ድጋፍ ተደርጎላቸዋል፤



ሰው ሰራሽ የአካል ድጋፍ የተበረከተላቸው ወገኖች

- 17 የተለያየ የአካል ጉዳት ያለባቸው የቴክኒክና ሙያ ተማሪዎች የት/ት መሳሪያዎችና ቴክኒካዊ ድጋፍ ተሰጥቷቸዋል፤
- በ32 ት/ቤቶች ትምህርት መዝጊያ ላይ ከ33 ሺህ በላይ ለሚሆኑ የማህረሰብ ክፍሎች ስለአካል ጉዳተኝነትና ተያያዥ ጉዳዮች የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት ተሰጥቷል፤
- 338 ሺ.ህ የሚሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ስለተላላፊ በሽታዎች፣ አካል ጉዳት፣ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ፣ አካትቶ ትምህርት... ወዘተ ጉዳዮች በወላይታ ዎጌታ ኤፍ.ኤም 96.6 ሬዲዮ በህጻን ለህጻን ክበባት፣ በት/ቤት አካል ጉዳተኞች ክበባትና ማህረሰብ ውይይት  አማካይነት ትምህርት ተሰጥቷል፤
- ለ300 ሺ.ህ የህብረተሰብ ክፍል በወላይታ ዎጌታ ኤፍ.ኤም. 96.6 ሬዲዮ ለ30 ደቂቃዎች በሚተላለፈው ፕሮግራም ስለአካል ጉዳት መረጃ ተላልፏል፤
- 702 (ወ-393 ሴ-309) ግለሰቦች በማህበረሰብ ውይይት አማካይነት በአካባያቸው ስለአካል ጉዳት ያላቸውን ግንዘቤ እንዲያዳብሩና ተያያዥ ችግሮችን እንዲያስወግዱ ተችሏል፤
- 1934 (ወ-1211 ሴ-723) ህጻናት በህጻን ለህጻን ከበብ አማካይነት ስለአካል ጉዳት ምንነትና ዓይነቶች፣ ከአካል ጉዳት ጋር ተያያዞ መጠቀም ስለሌለባቸው ቃላት ግንዘቤ እንዲያገኙ ተደርጓል፤
- 1249 (ወ-392 ሴ-857) የመንደር ቁጠባና ብድር ማህበር አባላት ስለአካል ጉደተኝነት እና ተያያዥ ጉዳዮች  የግንዛቤ ማስጨበጫ ትምህርት አግኝተዋል፤117 እናቶች ስለአካል ጉዳት ትምህርት አግኝተዋል፤
- 195 (ወ-157 ሴ-38) መሰረተ ማህበረሰብ ተሃድሶ ኮሚቴ አባላት አካል ጉዳተኞችን በልማት እንዴት ማካተት እንደሚቻል ትምህርት አግኝተዋል፤
- 140 (ወ-98 ሴ-42) ከአካል ጉዳተኞች ማህበራት፣ መያድ እና ከመንግስት ባለድርሻ መስሪያ ቤቶች የተወጣጡ ግለሰቦች በዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኞች ቀን አከባበር ስለአካል ጉዳት እና ተያያዥ ጉዳዮች የግንዘቤ ማስጨበጫ አግኝተዋል፤



የዓለም አካል ጉዳተኞች ቀን አከባበር በወላይታ ጉታራ አዳራሽ ወላይታ ሶዶ

◇ ለ419 (ወ-197 ሴ-222)ተሳታፊዎች በተለያየ ርዕስ 9(ዘጠኝ) የአቅም ግንባታ ስልጠና ተሰጥቷቸዋል፤

◇ 62 የመንደር ቁጠባና ብድር ማህበራትን በማደራጀት ከ195 ሺ.ህ ብር በላይ ማስቆጠብ ተችሏል፣ ከዚ.ህ ውስጥ 115ሺ.ህ የሚሆን ብር ለአባላት ብድር ተሰራጭቷል፤ በተጨማሪም ተከታታይ ድጋፍና ክትትል እየተደረገላቸው ይገኛል፤

◇ 222 አባላትን የያዘ የእናቶችን ክበባት በማቋቋም በየ15 ቀናት በመገናኘት ልምዶቻቸውን እንዲለዋወጡ እና ማህበራዊ ችግሮቻቸውን በራሳቸው መፍታት የሚችሉበት ባህል ዳብሯል፤

## 2. ወልማ በተቋማዊ ለውጥ ስራዎች

በዚህ ዘርፍ የወላይታ ልማት ማህበር የውስጥ ድርጅታዊ አቅሙን ለመገንባት የሰራተኛውን እውቀትና ክህሎት በስልጠና በማሳደግ፣ የልማት ስራዎችን በዘመነ መልኩ በጥራትና በፍጥነት ለማከናወን ከአባላቱ፣ ደጋፊዎቹና ለጋሽ ድርጅቶች በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ሃብት በማሰባሰብ፣ የገቢ ማስገኛ ተቋማትን በማደራጀትና በማጠናከር አቅም በፈቀደ መጠን እ.አ.አ ከ2016 - 2020 በሚተገበረው ስትራቴጂክ ፕላን መነሻነት ከምንጊዜውም በላይ በርካታ ይበል የሚያሰኙ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል፤ ዋና ዋና ተግባራትን ቀጥሎ እናያለን፡፡

### 2.1 በሰው ሃብት አስተዳደርና ልማት

የልማት ማህበሩ የሰው ሀብት አስተዳደርና ልማት አጠቃላይ የማህበሩን ሰው ሀይል አደረጃጀት ከማሟላት ባለፈ የደመወዝ ዋስትናውን ማረጋገጥ ብቻ ግቡ የሆነ ሰራተኛ ሳይሆን ለወላይታ ሕዝብ ኑሮ መሻሻል ወቅቱ የሚፈልገውን እውቀት ከክህሎት አቀናጅቶ ማህበሩ ከድህነትና ኋላቀርነት የተላቀቀ ወላይታን ለማየት ለያዘው የረጅም ጊዜ ራዕይ ስኬት ዛሬ ኃላፊነቱን ተሸክሞ መጓዝ የሚያስችል ትክሻ ያላቸውን ሰራተኞች ለመፍጠር የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን መስጠትና ሌሎች ዘርፈ ብዙ ተግባራትን ዓላማው አድርጎ የሚሰራበት ዘርፍ ነው፡፡

በዘርፉ በበጀት ዓመቱ የማህበሩ ነባሩ አስተዳደራዊ መዋቅር ጉድለት የሚስተዋልበት መሆኑ በዳሰሳ ጥናት በመረጋገጡ የተገልጋዮችንና የማህበሩ ሰራተኞች የሰጡትን አስተያየት መነሻ በማድረግ በስራ አመራር ቦርድ ውሳኔ የማህበሩ አስተዳደራዊ መዋቅር በጥልቀት እየተጠና ይገኛል፡፡

በዓመቱ 82 አዳዲስ ሠራተኞች በልማት ማህበሩ በተለያዩ ክፍት የስራ መደቦች ተመልምለው ማህበሩን ተቀላቅለው ከማህበሩ የሰው ሃብት አስተዳደር መመሪያ ጋርም ተዋውቀዋል፤ 20 ሰራተኞች ደግሞ በውስጥ ውድድር መስፈርቱን አሟልተው ተመድበዋል፤ 42 የኮንትራት ሰራተኞች ደግሞ የስራ ውል ኮንትራታቸው

የወላይታ ልማት ማህበር የሰው ሃይልና የትምህርት ደረጃ መረጃ

| ጾታ | 2ኛ ዲግሪ | ባችለር ድግሪ | ዲፕሎማ | ከዲፕሎማ በታች | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| ወ | 14 | 105 | 75 | 79 | 273 |
| ሴ | - | 18 | 41 | 95 | 154 |
| ድ | 14 | 123 | 116 | 174 | 427 |

በበጀት ዓመቱ 27 የማህበሩ ቋሚ ሰራተኞች የህክምና አገልግሎት እንዲያገኙ ማመቻቸትና እንዲሁም ሁሉም የማህበሩ ሰራተኞች በተገኙበት የሰራተኞች ቀን መከበሩ ዋና ዋና ተግባራት ሲሆኑ የተሻለ የስራ አፈጻጸም ላሳዩ የማህበሩ ሰራተኞች የማበረታቻ ሽልማት በመስጠት ብሎም የማህበሩን የሰው ሃብት አስተዳደር መመሪያ ጥሰው መገኘታቸው በልማት ማህበሩ የሕግ አማካሪ የተረጋገጠባቸው 21 ሰራተኞች ላይ እንደየጥፋታቸው ልክ ትምህርት ሊሰጡ የሚችሉ አስተዳደራዊ የማስተማሪያ እርምጃዎች ተወስደባቸዋል፡፡

## 2.2 ቢዝነስ ልማትና አስተዳደር

ይህ ዘርፍ ማህበሩ በአባላት መዋጮና በውጭ እርዳታ ላይ ካለው ጥገኝነት ደረጃ በደረጃ የሚላቀቅበትን መንገዶች በማጥናት አዋጪ በሆኑ የገቢ ማግኛ ዘርፎች ላይ በመሰማራት የማህበሩን የውስጥ አቅም በማጎልበት በራስ አቅም በዞናችን የልማት ተግባራትን የማከናወን አቅምን መፍጠር ዋና ግቡ አድርጎ የሚሰራበት ዘርፍ ሲሆን በቀጣዮቹ ዓመታት ደረጃ በደረጃ ሊከናወኑ የታቀዱ ከ300 ሚሊዮን ብር በላይ ካፒታል የሚያስፈልጋቸውን አዳዲስ የገቢ ማስገኛ ፕሮጀክቶች ለማከናወንም ታቅዶ ወደስራ ተገብቷል፡፡ ቀጥሎ ለዚህ ዓላማ ስኬት ከዚህ ቀደም ተቋቁመው ወደ ስራ የገቡ ተቋማት ያሉበትን ደረጃ በአጭሩ እናስቃኛችኋለን፡፡

### 2.2.1 ዳሞታ ኮንስትራክሽን ኩባንያ

የዳሞታ ኮንስትራክሽን ኩባንያ ልማት ማህበሩ ለአላማ ማስፈጸሚያ የሚውል ሃብት በራሱ አቅም ለማግኘት ይቻለው ዘንድ ባለፈው በጀት ዓመት ያቋቋማ የገቢ ማስገኛ ተቋም ሲሆን ኩባንያው ማንኛውንም ዓይነት የግንባታ ስራዎችን መስራት፣ የግንባታ ግብዓቶችን ማምረት፣ ከእንጨትና ከብረት የቤትና ቢሮ ዕቃዎችን ማምረት፣ ትልልቅ ማሽነሪዎችን ማከራየት ዋና ዋና ተግባራቱ ሲሆኑ ሌሎችንም ዘርፈ ብዙ ተግባራት በተቋቋመ አጭር ጊዜ ውስጥ በጥራት ያከናወነ ሲሆን የሚከተሉት ዋና ዋና ዎቹ ናቸው፡፡

- በሶዶ ከተማ ባለ ዘጠኝ ወለሉን የወላይታ ልማት ማህበር ማህበረሰብ ልማት ህንጻ እና ሐዋሳ ከተማ ባለ አራት ወለል የማህበረሰብ ልማት ሕንጻ በጥራት እየገነባ ይገኛል፤
- የልማት ማህበሩን እንግዳ ማረፊያ ህንጻ በጥራት አጠናቅቆ ለአገልግሎት አብቅቷል፤
- ለወላይታ ድቻ ስፖርት ክለብ ማዕድ ቤት በመገንባት ገንብቶ ለአገልግሎት አብቅቷል፤
- ሁለት የማህበረሰብ ኩሬ ገንብቶ አስረክቧል፤
- የድንጋይ መፍጫ ማሽን በመትከል ከ256 ኪዩቢክ ሜትር በላይ የተለያየ መጠን ያለው የግንባታ ጠጠር በማምረት ለራሱ ግንባታና ለገበያ አቅርቧል፤
- የኢኮኖሚ አቅማቸው ደካማ ሆኖ በወልማ የተለያዩ ፕሮጀክቶች ለተደራጁ ወጣት ማህበራት የመስሪያና የሽያጭ ቦታ ገንብቶ አስረክቧል፤
- በዳሞት ጋሌ ወረዳ የአንድ አርሶ አደሮች ማሰልጠኛ ማዕከል ግንባታ ገንብቷል፤




የጠጠር ማምረቻ ማሽን (አባላ ማራቃ)

- የቶሜ ጌሬራና ላሾ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች አድሶ አስረክቧል፤
- የወላይታ ዞን 3 ሴክተር መ/ቤቶች አድሶ አስረክቧል፤
- በዳሞት ጋሌ ወረዳ አንድ አርሶ አደሮች ማሰልጠኛ ማዕከል ግንባታ ገንብቷል፤

በበጀት ዓመቱ ከግንባታ ስራው በተጨማሪ ኩባንያው የተለያዩ ማሽኖችን በማከራየት፣ የእንጨትና ብረታብረት ምርቶች በማምረትና የግንባታ ግብዓቶች ለገበያ በማቅረብ ከ5.9 ሚሊዮን ብር በላይ ገቢ ማግኘት አግኝቷል፤

## 2.2.2 ወላይታ ጉታራ ስልጠና ማዕከል

የወላይታ ጉታራ ስልጠና ማዕከል ልማት ማህበሩ ካሉት የገቢ ማስገኛ ተቋማት ቀደም ብሎ የተቋቋመው ነው፤ ማዕከሉ ለበርካታ ቋሚና ኮንትራት ሰራተኞች የስራ ዕድል በመፍጠር በዞናችን ለሚስተዋለው የስራ አጥነት ችግር የራሱን አስተዋጽዖ አበርክቷል፡፡

ስልጠና ማዕከሉ ሃገራዊ፣ ክልላዊና ዞናዊ መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት የሚዘጋጁ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያና ሐይማኖታዊ ስብሰባዎችን፣ ስልጠናዎችን፣ ወርክሾፖችን እና ሌሎች ኩነቶችን የሚያስተናግዱ ምቹ አዳራሾች ከዘመናዊና ባህል ምግቦች፣ ክነጻ ፈጣን የኢንቱርኔት አገልግሎቶች አካቶ የያዘ ሲሆን ማዕከሉ ባለፈው በጀት ዓመት ለተለያዩ ግብዓት ግዥ ብር 16,784,792.57 ወጪ በማድረግ የዕለት ተዕለት ስራዎችን መስራት ሲሰራ ቆይቷል፡፡ በዓመቱ ብር 26,164,756 ገቢ ለማግኘት አቅዶ 23,072,164 ገቢ አግኝቷል፤ ከዚህም ብር 6,287,371.51 ትርፍ ማግኘት ተችሏል፤

## 3. አባላት ልማትና ሃብት አሰባሰብ

የወላይታ ልማት ማህበር በዚህ ዘርፍ ለልማት የሚሆን ሀብት በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ ከአባላትና ለጋሾች በማሰባሰብ የማሰባሰብ ተግባር ያከናውናል፡፡ ከዚህ በታች በዘርፉ በበጀት ዓመቱ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ተዘርዝሯል፡፡

| የአደረጃጀት ዓይነት | የአባላት ብዛት |
|---|---|
| አርሶ አደር | 7,431 |
| የመንግስት ሰራተኞች | 5,700 |
| ነጋዴ | 533 |
| ተማሪ | 15,305 |
| ኮርፖሬት አባላት | 78 |
| ልዩ አባላት | 25 |
| ሌሎች አባላት | 6429 |
| ድምር | 35,501 |

**በዓመቱ 1 የአባላት ጠቅላላ ጉባኤና በማህበሩ 14 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የአባላት ጠቅላላ ጉባኤዎች ተካሂደዋል፤ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የድጋፍና ክትትል ስራ ተሰርቷል ወርሃዊ ግምገማዎችም ተካሂደዋል፡፡ አጠቃላይ በበጀት ዓመቱ** 35,501(ሰላሳ አምስት ሺህ አምስት መቶ አንድ) አዲስ አባላትን ማደራጀትም ተችሏል፡፡ ማህበሩ የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ኤጀንሲ ባወጣው የመልካም ስራ አፈጻጸም ተወዳድሮ በማሸነፍ **1 Rav 4 Toyota Model አውቶሞቢል ማግኘት ችሏል፤**

**በበጀት ዓመቱ ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ብር 88,403,992.58 (ሰማኒያ ስምንት ሚሊዮን አራት መቶ ሶስት ሺህ ዘጠኝ መቶ ዘጠና ሁለት ብር ከ 58/100 ብር ብቻ) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተሰብስቦ በዞኑ ልማት ላይ ውሏል፡፡**

| **የገቢ ምንጭ** | **መለኪያ** | **መጠን** |
|---|---|---|
| የአባልነት መዋጮ | ብር | 17,621,567.12 |
| ከለጋሽ ግለሰቦችና ድርጅቶች | | 46,984,557.270 |
| ወላይታ ታላቁ ሩጫ | | 633,296 |
| ከወላይታ ሊቃ ት/ቤት | | 1,339,971.79 |
| ከወላይታ ጉታራ ስልጠና ማዕከል | | 2,394,184 |
| ቀድሞ ቃል የተገባና ሳይሰበሰብ የቆየ | | 16,389,674.4 |
| የጉልበትና ዕውቀት አስተዋጽኦ | | 3,015,742 |
| ገቢ ማስገኛ ትዕይንት | | 25000 |
| **ድምር** | | 88,403,992.58 |

## 4. ማህበሩ በእቅድ ዝግጅት፣ ክትትልና ግምገማ

ልማት ማህበሩ ለነባር አጋር ድርጅቶችና ለአዳዲስ ረጂ ድርጅቶች ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን አዘጋጅቶ ይልካል፤ በስራ ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶችን አፈጻጸም ይገመግማል፤ እንደፕሮጀክቱ የበጀት መጠን ደግሞ ሪፖርቶችን አጠናቅሮ ስልጣን ላለው የመንግስት ባለድርሻ መ/ቤቶች መላክ በዘርፉ የሚከናወኑ ተግባራት ሲሆኑ በበጀት ዓመቱ የሚከተሉትን ዋና ዋና ተግባራት አከናውኗል።

- የወላይታ ልማት ማህበር የ2017 በጀት ዓመት ሪፖርት በማዘጋጀት ለሚመለከታቸው አካላት ተዳርሷል፤
- የልማት ማህበሩን ስትራቴጂክ ፕላን መነሻ በማድረግ ከተቋማት፣ ዳይሬክቶሬቶችና የስራ ክፍሎች የመጡ ዕቅዶች ተጠናቅረው በበጀት ዓመቱ መጀመሪያ ወደስራ ተገብቷል፤
- የልማት ማህበሩን የዓመት፣ ግማሽ ዓመት፣ ሩብ ዓመትና ወርሃዊ የሩብ ዓመት ሪፖርቶችን ከዳይሬክቶሬቶች፣ ስራ ክፍሎችና ተቋማት አሰባስቦ በማጠናቀር ለማህበሩ ስራ አመራር ቦርድና ለሚመለከታቸው አካላት አቅርቧል፤
- 7 የሩብ ዓመት፣ 4አጋማሽ፣ እና 2 የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ሪፖርቶች ኃላፊነት ለተሰጠው የመንግስት ተቋማት ተዳርሰዋል፤
- በልማት ማህበሩ እና ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ መካከል የማህበረሰብ ልማት ስራዎችን በጋራ መስራት የሚስችል የመግባቢያ ስምምነት ሰነድ ተዘጋጅቶ ወደስራ ተገብቷል፤
- 11 የተለያዩ ፕሮጀክቶችና ሌሎች ተግባራት ክትትልና ግምገማ ስራ ተሰርቶ አስፈላጊው ግብረ መልስ ተሰጥቶባቸዋል።
- በልማት ማህበሩ የሚከናወኑ የግንባታ ስራዎች የድጋፍና ክትትል ስራ፤
- ከማህበሩ የትኩረት አቅጣጫዎች ጋር የሚጣጣሙ ፕሮጀክት ፕሮፖዛሎችን በማዘጋጀት ለለጋሽ ድርጅቶች ተልኳል፤
- ከወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር የልማት ማህበሩ በዞኑ ያበረከተውን በጎ ተጽዕኖ የመገምገም ስራን እያስተባበረ ይገኛል።

## 5. ወልማ በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ዘርፍ

ወልማ በኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ዘርፍ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም የተለያዩ ስራዎችን መስራት የሚያስችሉ ሶፍትዌሮችን የማበልጸግ፣ ኔትወርክ ዝርጋታ በማካሄድ፣ የተበላሹ ኮምፒውተሮችና ሌሎች ኮምፒውተር ነክ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን በመጠገን አገልግሎት እንዲሰጡ ማስቻልና የውስጥ እና የውጭ የሕዝብ ግንኙነት ስራዎችን ይሰራል። በዚህ ዘርፍ የተከናወኑ ዋና ዋና ተግባራት ቀጥሎ ተዘርዝረዋል።

### 5.1 በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት

- ከብር 40ሺህ በላይ የሚገመት የተለያዩ ሞዴል ኮምፒውተሮች፣ ፎቶ ኮፒና ማባዣ ማሽን፣ ፕሪንተር፣ ላፕቶፕ፣ የኔትወርክ ዝርጋታና ጥገና እንዲሁም ሌሎች የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ጥገና ተከናውኗል፤
- የሂሳብ ስራ ለሚሰሩ የስራ ክፍሎች ለስራቸው አስፈላጊ የሆኑ ሶፍትዌሮች ዕድሳት ተደርጓል የዕለት ተዕለት ስራቸውን በአግባቡ እንዲያከናውኑ የማስቻል፣ የመረጃ ፍሰቱንም የመቆጣጠር የፋይሎችን ደህንነት የመጠበቅ ስራ ተሰርቷል፤
- ለማህበሩ ስራ የሚያገለግሉ የአበላት ምዝገባ እና ንብረት ምዝገባ ሲስተሞች በራስ አቅም በማበልፀግ ለሚመለከታቸው የስራ ክፍሎች ሰራተኞች የስራ ላይ ስልጠና ተሰጥቷቸው ወደስራ ተገብተዋል፤ የሰው ሃብት ልማት ሲስተምም በማበልጸግ ሂደት ላይ ይገኛል፤
- ወቅታዊ አዳዲስ መረጃዎችና ዜናዎች በማህበሩ ድረ-ገጽ ላይ እየተጫኑ ለህብረተሰቡ ይፋ እንዲሆን ተደርጓል፤

- የማህበሩን መረጃዎች ደህንነት ለማስጠበቅ ፈቃድ ያለው ጸረ-ቫይረስ ሶፍትዌሮች ለሰርቨሮችና ልዩ ትኩረት ለሚሻቸው ኮምፒውተሮች ተጭኗል፤
- ለወላይታ ጉታራ ስልጠና ማዕከል እና ወላይታ ዎጌታ ሬዲዮ የገመድና ገመድ አልባ ኔትወርክ ዝርጋታ ተከናዉኗል፤
- የማህበሩን የመልዕክት ልውውጥ የማስተዳደርና የመረጃ ቋቱንም ደህንነትና ልውውጥ ስርዓት ፍሰት የመቆጣጠር ስራ ተሰርቷል።

## 5.2 የሕዝብ ግኑኝነት ስራዎች

- የማህበሩን ድረገጽና ማህበራዊ ሚዲያዎች በመጠቀም በትኩረት መስኮቹ የሚያከናውናቸውን ተግባራት ለህብረተሰቡ በወቅቱ በማድረስ አባላት መረጃ እንዲያገኙ ምቹ ሁኔታ ተፈጥሯል።
- በዓመቱ በተለያዩ ሕዝባዊ በዓላት የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክቶችና መልካም ምኞቶች መግለጫዎቸች በልማት ማህበሩ ማህበራዊ ሚዲያዎች እና ሌሎች ሚዲያዎች አማካይነት ለአባላት ተላልፈዋል፤
- የማህበሩ ዋና ዋና የልማት ስራዎች የሚዳሰሱበት ሳምንታዊ የ30 ደቂቃ የሬዲዮ ፕሮግራም ለሕዝብ በተከታታይ እየተላለፈ ይገኛል።
- ወቅቱን የጠበቀ የኤልክትሮኒክስ መልዕክቶች ልውውጦች በማህበሩ የግል የመልዕክት ልውውጥ ቋት አማካኝነት ተከናውኗል።

### 5.2.1 የማህበረሰብ ሬዲዮ

ይህ ሬዲዮ ጣቢያ ወላይታ ልማት ማህበር የአካባቢውን ህብረተሰብ የመረጃ ፍላጎትና የረጅም ጊዜ የሕዝባችንን በራስ አንደበት የሚናገሩበት ሚዲያ ጥያቄ መነሻ በማድረግ ከወላይታ ዞን አስተዳደር ጋር በመተባበር 60 ከመቶ ስርጭቱን በአካባቢያዊ ርዕስ ጉዳዮች በራሳችን ቋንቋ እና 40 ከመቶውን አገር አቀፍና አለም አቀፍ መረጃዎች አካቶ በአማርኛ በተመሳሳይ ርዕስ ጉዳዮች ትኩረቱን በማድረግ ሕብረተሰቡን በቀን ለ13 ሰዓታት የሚያገለግል ጣቢያ አቋቁሞ ለኅብረተሰቡ ከማበርከት ባለፈ ጣቢያውን በፋይናንስና በሌሎችም ዘርፎች ድጋፍ እያደረገ ይገኛል:

ከዚህ ሬዲዮ ጣቢያ ጋር በመተባበርም 6 በወላይታ ልማት ማህበር የትኩረት አቅጣጫዎች የተሰሩ ፕሮግራሞች ለህብረተሰቡ ተሰራጭቷል፤ ሌሎችንም የማህበሩን ተግባራት ለአባላት በየወቅቱ ተዳርሷል፤ ሳምንታዊ የ30 ደቂቃ የሬዲዮ ፕሮግራምም ከጣቢያው ጋር በመተባበር በቋሚነት እየተሰራበትም ይገኛል።

በቀጣይም ከተደራሽነትና ከጥራት ጋር በሕብረተሰቡ ዘንድ የሚነሳውን ጥያቄ ለመፍታት ከዞኑ መንግስትና ከተለያዩ ተቋማትና ከሬዲዮ ጣቢያው ቦርድ አባላት ጋር በመተባበር ችግሩን ለመፍታት ጥረት እያደረገ ይገኛል።

### 5.2.2 ሕትመቶች

- ሳምንታዊ፣ ወርሃዊ፣ የሩብ ዓመትና ግማሽ ዓመት ዜናዎችና ዓመታዊ መጽሔቶች ታትመው ለአባላት ተሰራጭቷል።
- በልማት ማህበሩ የሚከናወኑ ተግባራትን ለማስተዋወቅ ከመስክ የተሰበሰቡ ምስሎች ተቀናብረው በወላይታ ጉታራ ስልጠና ማዕከል ለህዝብ እንዲታይ ተደርጓል፤
- 1000 ቅጂ የወላይታ ሊቃ ት/ቤት ዓመታዊ መጽሄት በማሳተም ለህብረተሰብ ተሰራጭቷል፤
- ማህበሩን በሰፊው ለማስተዋወቅ 1000 ኮፒ የልማት ማህበሩ ሎጎ፣ 1000 ቅጂ የአጋር ድርጅቶች ሎጎ እና 1000 ቅጂ የማህበሩን የትኩረት አቅጣጫዎችና ሌሎች መረጃዎችን የያዘ ማስታወሻ ደብተር ታትሞ አገልግሎት ላይ ውሏል፤

- 55 ሳምንታዊ ዜናዎችና 3 የሩብ ዓመት ዜናዎች ተሰርተው በልማት ማህበሩ ማህበራዊ ሚዲያ፣ ድረ-ገፅ እና የማስታወቂያ ቦርዶችን በመጠቀም ለሕዝብ ተዳርሷል።

- የማህበሩን ስራ የሚያሳዩ ሁለት ትልልቅ ዲጂታል ባነሮች ታትመው በሶዶ ከተማ ተሰቅለዋል፣

- በየጊዜው የተላለፉ የማህበሩ ማኔጅመንት ውሳኔዎች ቃለጉባኤዎች ታትመው ለወደፊት ማጣቀሻነት ተሰንደዋል፣

- 39 የተለያየ መጠን ያለቸው ባነሮች ታትመው በአገልግሎት ላይ ውለዋል፣

- የልማት ማህበሩን እ.አ.አ የ2017 በጀት ዓመት ክንውን የሚያሳይ መጽሄት ታትሞ ለአባላት

- በተለያየ ርዕስና ቁጥር 6 ዓይነት ብሮሽሮች ለወላይታ ዎጌታና መሰረተ ማህበረሰብ አካትቶ ልማት ፕሮጀክት ታትመው አገልግሎት ላይ ውለዋል፣

### 6. በስራ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮች

- ተግባራትን ለማከናወን በቂ በጀት አለመኖርና የህዝብ ጥያቄን መመለስ አለመቻል፣
- ስራዎችን በወቅቱ ለማከናወን በቂ የመስክ ተሽከርካሪ አለመኖር
- በሀገሪቱ የተፈጠረው የጸጥታ ችግር ልማት ማህበሩ በሐዋሳ የጀመረውን የማህበረሰብ ልማት ህንጻ ማስቀጠል አለመቻል፣
- በአንዳንድ ወረዳዎች የሚገኙ የማህበሩ አስተባባሪዎች ቁርጠኝነት ማነስ፣
- በአንዳንድ ወረዳዎች የሚገኙ የሒሳብ ሰራተኞች ዘንድ ከመንግስት ሰራተኞች የተሰበሰበውን የማህበሩን ሃብት ወዲያውኑ ለማህበሩ ያለማስተላለፍ፣

ለወላይታ ሕዝብ ለውጥ፣ ዕድገትና ብልጽግና ሌት-ተቀን የሚተጋው ከእናንተው፣ ለእናንተ በእናንተ በሚሰራውና አንደበታችሁ የሆነውን የወላይታ ማህበረሰብ ሬዲዮ ዎላይታ ዎጌታ ኤፍ ኤም 96.6 ያዳምጡ፣ ይናገሩበት፣ ይሳተፉበት።

ትጋትና ታማኝነት ለብልጽግና!



ባለፉት 18 ዓመታት በወላይታ ልማት ማህበር በማህበረሰብ ተሃድሶ ልማት ፕሮግራም የሪፌራል ቀዶ ጥገና ሕክምና ተደርጎላቸው፣ የአካል ድጋፍና ተሽከርካሪ ልገሳ ተደርጎላቸው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸውን ከማህበረሰቡ ጋር በዕኩል ደረጃ እንዲያከናውኑ ካስቻላቸዉ 10,800 ወገኖቻችን በከፊል፡፡

# WODA
# WOLAITTA DEVELOPMENT ASSOCIATION

ወላይታ ልማት ማህበር

Wolaytta Dichaa Amuwaa
Wolaitta Development Association

**Vision:** WODA envisions transformed Wolaitta from backwardness and poverty.

**Mission:** We are committed to work for socio-economic development of Wolaitta by soliciting resource from the community, non-governmental organizations, supporters and other sources and enhancing active community participation to initiate and sufficiently work on demand-driven development programs in the areas of Human capital development, Sustainable livelihood security and Integrated Health.

**Values:** WODA values constitute: transparency, efficiency and effectiveness, equity and fairness, gender sensitivity, inclusiveness. community participation, accountability and responsiveness

**Thematic Areas:**
1. Human Capital Development
2. Sustainable Livelihood Security
3. Integrated Health


TELEPHONE: +251-46-551-36-92
+251-465-51-21-88
+251-465-51-52-42
FAX: +251-46-551-00-37
P.O.BOX: 001 WOLAITTA SODO ETHIOPIA
email:wda@ethionet.et/wolaitta@gmail.com

**Website: ...www.wolaittada.org**

*Social Medias:* www.facebook.com/wolaittadevelopmentassociation
www.youtube.com/WODA2001
www.twitter.com/wolaitta


WolayttaWorqaaMayzzana!

## OUR FUNDING PARTNERS